አሐዱ ባንክ Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com


# ንግድና ልማት

ግንቦት 2015 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com


## አዲስ ቻምበር እና ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ሰነድ ተፈራረሙ



**በሰናይት እሸቱ**

በአዲስ ቻምበር ጽ/ቤት በተከናወነው የፊርማ ስነ ስርአት ላይ ስምምነቱ የምክር ቤቱን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም አቅሙን ለመጠቀም እንደሚያግዝ ተጠቁሟል።

የአዲስ ቻምበር ዋና ጸሃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም እንዳሉት ምክር ቤቱ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን ለንግዱ ማህበረሰብ የሚሰጥ እና ጥናትን መነሻ ያደረጉ የተሟሉ የቢዝነስ መረጃዎች የሚገኙበት በመሆኑ ስምምነቱ የሁለትዮሽ ተጠቃሚነትን ሊያጠናክር እንደሚችል አንስተዋል።

የፋና ብሮድካስት ኮርፖሬት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አድማሱ ዳምጠው በበኩላቸው ተቋማቸው በመረጃ የበለጸገ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚሰራ መሆኑን አንስተው መረጃዎቹ በእውቀት ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዲችሉ ከማድረግ አኳያ አዲስ ቻምበር ባለው እምቅ አቅም ሊያግዛቸው እንደሚችል ተናግረዋል።

በተጨማሪም አዲስ ቻምበር የሚያከናውናቸውን ተግባራት ብቻ ሳይሆን እንደ ሃገር የሚከናወኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች ቀጥተኛ እና በእውቀት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ መስራት ላይ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑንም ጠቁመዋል።

በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው ስምምነትም ወደ መሬት ወርዶ ተግባር ላይ እንዲውል ኮሚቴ በማዋቀር እና እቅዶችን በማውጣት በመጭው 2016 ዓ.ም ተግባር ላይ እንዲውል ስምምነት ላይ ተደርሷል።

## ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ ተግባራዊ ማድረግ ለንግድና ኢንቨስትመንት ማደግ ወሳኝ ድርሻ አለው




**በከፍያለው ዋሲሁን**

በእንግሊዘኛው Responsible Business conduct (RBC) ይሉታል ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ መከወን እንደማለት ነው በግርድፉ ወደ አማርኛ ስንመልሰው። ይህ ዘመናዊ የንግድ ስራ አመራር ለኢትዮጵያ አዲስና ያልተለመደ ፅንሰ ሃሳብ ነው። ይህ ፅንሰ ሃሳብ በዋናነት የሚያጠንጥነው አንድ ነጋዴ ለራሱና ለሚሰራው ንግድ ታማኝ በመሆን ህግን አክብሮ የሚሰራበት መንገድ ነው። ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ ኃሳቡ አንድ የንግድ ድርጅት የንግድ ስራውን በሚከውንበት ወቅት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ማህበረሰቡንና አካባቢውን ከሚጎዱ ያልተገቡና ከሞራል ያፈነገጡ አሰራሮች ተቆጥበው የሚሰሩበት የንግድ ስነ- ምግባር መመሪያ ማለት ነው።

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

MIDROC INVESTMENT GROUP

Elfora Agro Industries P.L.C.
A Member of the MIDROC Investments Group Companies



ELFORA STANDS FOR NATURAL & QUALITY PRODUCTS !

Phone: +251-116-46-10-79, +251-116-45-03-61
Fax: +251-116-45-05-03
E-Mail: elforamarketing@gmail.com
mohzeki73@gmail.com
Website: midrocinvestmentgroup.com/en

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ

## ፶ዐኛ ዓመት እትም

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirma0357@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
እስራኤል ማንአየ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ግንቦት 2015 እትም

# ርዕሰ አንቀጽ

## ሃላፊነት የተሞላበት የቢዝነስ አሰራር ለዘላቂ ልማት

በአገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዘመናዊ የቢዝነስ አመራር አስተሳሰቦች መካከል ሀላፊነት የተሞላበት የንግድ አሰራር 'Responsible Business Conducts (RBC)' ከዘመናዊ የንግድ ሥራ አመራር ጋር ተያይዞ ይነሳል። ሃላፊነትን የተላበሰ የቢዝነስ አሰራር በውጪው ዓለም የተለመደ እና የቆየ አሰራር እንደሆነ ይነገራል። የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤትም ይህን ዘመናዊ አስተሳሰብ ለአባላቶቹ  በተለያዩ መንገዶች እያስረጸ ይገኛል።

ይህ አሰራር ሁለት ጉዳዮችን በዋናነት ያካትታል። የመጀመሪያው ዘላቂ ልማት ለማምጣት የንግድ ድርጅቶች ለኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ እና አካባቢያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያግዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በንግድ ስራ ውስጥ ምርት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ሂደት ላይ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ሊያደርሱ የሚችሉትን ተጽዕኖዎችን መቀነስ የሚለው ነው።

ስለዚህ አንደኛው የንግድ ድርጅቶች ለዘላቂ ልማት የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ የሚመለከት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በአካባቢው፣ በማሕበረሰቡ ወይም በኢኮኖሚ ላይ ኩባንያዎች ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመቀነስ የሚሰሩ ሥራዎቸን ያካትታል።
እርግጥ ኩባንያዎች ሁላችንም የምንፈልጋትን አለም በመፍጠር ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ እና ድርጅቶቹም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊሸጋገሩ የሚችሉት ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ሲሰሩ መሆኑ እሙን ነው።

ስለዚህ ንግድ የአጭር ጊዜ ትርፍ ብቻ ሆኖ አንድ ኩባንያ ዛሬ ታይቶ ነገ እንዳይጠፋ እና ዘላቂ ሆነው በንግድ ውስጥ እንዲቆዩ ኃላፊነት በተሞለበት የንግድ ሥራ ማከናወን አለባቸው ማለት ብለን እናምናለን።
በባህላችን እንደሚባለው ‹የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው› አይነት ትርፍ ላይ ብቻ አልሞ መነገድ አሁን በዘመናዊው አለም ላይ አያስኬድም።

የዚህ ሃሳብ ማጠንጠኛ ንግዱ እንዴት ነው የሚሰራው?፤ የት ነው የሚሰራው?፤ በምን መንገድ ነው የሚሰራው? የሚሉትን መሰል ጉዳዮች ሁሉ ታሳቢ ማድረግ አለበት። ይህም ማለት የኩባንያው እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ምን ተጽእኖ ያመጣል?፤ ማሕበረሰቡን በምን መልኩ ይጠቅማል ወይም ይጎዳል? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን በደንብ የማጥራትና የኩባንያው አካሄድ የሃገሪቱን ሕጎች የሚያከብር እና ሕብረተሰቡ ከኩባንያው የሚጠብቀውን ያገናዘበ መሆን አለበት። ስለዚህ አንድ ኩባንያ ባለንበት ዘመን ዘላቂ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊሸጋገር የሚችለው በማንኛውም መንገድ ማትረፍ ስለቻለ ብቻ አይደለም።

በሌላ በኩል ኃላፊነት የተሞላበት የንግድ ስራ ከንግድ ድርጅቱ አሰራር ውጭ ሆኖ የሚታሰብ ሳይሆን አንድ የንግድ ድርጅት ከመጀመሪያው ስትራቴጂውን ሲቀርጽ፣ ንግድ ውስጥ ሲገባና ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ሁሉ አብሮ አጣጥሞ ተከትሎት ሊተገብረው የሚገባ ጉዳይ ነው።
ስለዚህ ኃላፊነት የተሞላበት የንግድ ስራ ኩባንያዎች በበጎ ፈቃደኝነት የሚያደርጉት ብቻ ሳይሆን ለህልውናቸው መሠረት የሆነ ሕጉም የሚጠብቅባቸው ኃላፊነት ሲሆን ይህንን አለመከተል የሕግ ተጠያቂነትን ያመጣል።

ስለሆነም ማንኛውም ድርጅት ለወድድር ብቁ ሆኖ መቅረብ ካስፈለገው የኩባንያ ኃላፊነት የተሞላበት የንግድ ሥራን ተግባራዊ ማድረጉ በራሱ ከሌሎች ኩባንያዎች በተሻለ ተወዳዳሪ እንዲሆን ያስችለዋል።
በዚህም ኩባንያው በደንበኞቹ፣ በሠራተኞቹ እንዲሁም በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ተቀባይነትና መልካም ስም እንዲኖረው ይረዳዋል። ስለዚህ በአካባቢው ካሉት ተመሳሳይ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች መካከል ሕብረተሰቡ የሚመርጠው የዚያን ድርጅት ምርቶች ወይም አገልግሎቱን ይሆናል። ስለዚህ የዚህ ኩባንያ የወደፊት ዕድገቱም ሆነ ዘላቂነቱ በሠራተኞቹ፣ በአካባቢው ነዋሪዎች እና በደንበኞቹ ላይ የተመሠረተ ስለሚሆን የሶስቱም አካላት ጥምር ድጋፍ የድርጅቱን ተወዳዳሪነትና ቀጣይነት ያረጋግጣል። አዲስ ቻምበርም ለአባል ኩባንያዎቹ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ የንግድ ስራቸውን እንዲያካሂዱ የሚግዙ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የስልጠና ፕሮግራሞችን እየሰጠ ይቀጥላል።

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤትና ሳክ ቢዝነስና ፐርሰናል ዴቨሎፐመንት አብረው ለመስራት የሚስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ

**በአሸናፊ ምትኩ**

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከተቋቋመባቸው አላማዎች አንዱ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎችን ለንግዱ ማህበረሰብ ማዳረስ ሲሆን ይህ የምክር ቤቱ አገልግሎት ኩባንያዎች ብቃት ባለው አመራር እንዲመሩና ዘላቂነት ያላቸው እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ የዚህ አንዱ አካል የሆነውና ምክር ቤቱ በቀጣይ ለሚተገብራቸው ስልጠናዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሚስችለውን ስምምነት በስልጠናና ምርምር ዘርፍ ከአስራ አምስት አመት በላይ ልምድና ተሞክሮ ካለው ከሳክ ቢዝነስና ፐርሰናል ዴቨሎፐመንት ጋር ተፈራርሟል፡፡ ይህ ስምምነት በተለይም ልምድና እውቀትን መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎች ለንግዱ ማህበረሰብ እና ለስራ ፈጣሪዎች በማዳረስ የንግድ



አመራር ክፍተቶችን ለመሙላት ትልቅ አጋጣሚ ነው በማለት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በስምምነቱ ወቅት ተናግረዋል፡፡ እንዲህ አይነት የትብብር መስኮች የምክር ቤቱን የስልጠና ተደራሽነት ከማስፋፋት ባለፈ ምክር ቤቱ በስራ ፈጠራ፣በፋይናንስ ተደራሽነት እንዲሁም በሌሎች አገልግሎቶች ዙርያ የሚያደርገውን ቀጣይ እንቅስቃሴዎች እንደሚያግዝ ዋና ጸሀፊው አክለው ተናግረዋል፡፡ ይህ ስምምነት በእውነት ላይ የተመሰረተ የቢዝነስ አመራርን ተደራሽ በማድረግ ወጣቶች በስራ ፈጠራ የሚደርጉትን እንቅስቃሴ መደገፍ እንደሚያስችል የሳክ ቢዝነስና ፐርሰናል ዴቨሎፐመንት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ዶ/ር አደራ አብደላ የመግባቢያ ሰነዱ በተፈረመበት ወቅት ተናግረዋል፡፡

በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረሰው ስምምነት በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚደረግ የተገለጸ ሲሆን በተለይም ለየት ያለ የቢዝነስ አመረራ ስልጠናዎች እና መድረኮች የሚመቻቹበት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መሆን ከቻለ በቢዝነስ አመራር በኩል የሚታዩ ክፍተቶችን በመሙላት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ተብሏል፡፡

# አረንጓዴ የኢኮኖሚ ልማትን ለማሳካት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ

**በሰናይት እሸቱ**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ንግድ እና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እንዲሁም ለንግዱ ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃዎች እንዲደርሱ ጥረት ያደርጋል፡፡ በተለይ የንግዱ ሕብረተሰብ ወቅታዊ ንግድ ነክ መረጃዎችን እና ወቅቱ የሚጠይቀውን አዳዲስ ዘመናዊ አሰራሮች ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ይንቀሳቀሳል፡፡ ንግድ ምክር ቤቱ ከዳኒሽ ኢንዱስትሪ ኮንፌዴሬሽን ጋር በመተባበር የንግዱ ህብረተሰብ በአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ፣በኩባንያ መልካም አስተዳደር እና ማሕበራዊ ኃላፊነቱን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲወጣ ማስቻልን ከግምት ውስጥ ያስገባ ስልጠና ለምክር ቤቱ ሰራተኞች ሰጥቷል፡፡ በተዘጋጀው ስልጠና ላይ የንግዱ ማህበረሰብ ሃላፊነት የሚታይበት እንዲሁም አረንጓዴ የንግድ ስራን እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል፡ ተረፈ ምርትን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የመሳሰሉ ቢዝነሶች ሚና እና ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት ዘዴዎች ላይ ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ በስልጠናው አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ዴንማርክ የምታከናውናቸውን ተግባራት ለማሳያነት የቀረበ ሲሆን በሃገራችንም በተለይ በምክር ቤቱ በተካሄደ ጥናት ተረፈ ምርትን መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ዘርፍ (Recycle business) ተገቢው ማበረታቻ እና ድጋፍ ከተደረገለት ብዙ ሥራ ፈጣሪዎችን ማሳተፍ የሚችል ትልቅ የቢዝነስ ዘርፍ መሆኑ ተጠቁሟል ፡፡ ሃላፊነት የተሞላበት ንግድን ከመከወን አንጻር ለንግዱ ማኀበረሰብ የአረንጓዴ ሽግግር (Green transition) አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ባደረገው ስልጠና ላይ አዲስ ጽንሰ ሃሳብ በሆነው በተዛማች ትርጉሙ ኡደታዊ ምጣኔ ሃብት(circular economy) ላይም ውይይት ተካሂዷል፡ በዚህም በአነስተኛ እና በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ስራ ፈጣሪዎችን በገንዘብም ሆነ በስልጠና በመደገፍ በዘርፉ እንዲሰማሩ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡

# የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ከአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ ለመሥራት ሥምምነት ተፈራረመ



የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ከአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኀበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ ለመሥራት ሥምምነት ተፈራረመ፡፡

ሥምምነቱን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ነጋሲ አምባዬና የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኀበራት ምክር ቤት ዋና ጸኃፊ አቶ ሺበሺ ቤተ-ማሪያም ፈርመውታል፡፡

ሥምምነቱን በተለይም ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያሳልጡ ሥራዎችን በጋራ ለመሥራትና ምክር ቤቱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት የበለጠ ለማስተዋወቅ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው፡፡ ተቋማቱ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ላይ የሚደጋገፉ ሲሆን ቶክሾውና ውይይቶችን በማዘጋጀት፣ በጥናትና ምርምር ተግባራት ላይ የሚተባበሩ መሆኑንም በሥምምነቱ ላይ ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኀበራት ምክር ቤት ዋና ጸኃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማሪያም እንደገለጹት ምክር ቤቱ ከተለያዩ አገራት ጋር የንግድ ግንኙነቶችን ማድረግ፣ የንግድ ትርኢቶች ማካሄድ፣ በውጭ አገራት ፎረሞችን ማከናወንን ጨምሮ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፡፡

ከዚህ ባሻገርም ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑና ጥናት ላይ የተመሰረቱ አውደ ጥናቶች፣ ሴሚናሮችና ጉባኤዎች ምክር ቤቱ እንደሚያካሂድ ጠቁመው እነዚህ ሁሉ ሥራዎች በአግባቡ በመገናኛ ብዙኃን በሚጠበቀው ደረጃ ተደራሽ እየሆኑ አይደለም ብለዋል፡፡

**ወደ ገጽ 11 ዞሯል**

# የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት እድሎችና ተግዳሮቶች...




የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት ( OECD ) ትርጓሜ የመንግስት ግዥ በመንግስት እና በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ ተቋማት ምርቶች( ሸቀጦች) ፣ አገልግሎቶች እና ስራዎች ግዥርን ይመለከታል።በመንግስት ተቋማት ውስጥ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም የተቀላጠፈና ክፍት ፣ ግልፅ ፣ ፈጠራ የታከለበት እና አሳታፊ የፖሊሲዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በመደገፍ እምነት የሚጣልበት መንግስት እንዲኖር የሚስችል ነው። ከዚህ አንፃር የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን በመንግስት ግዥዎች ውስጥ መጠቀም ተብሎ የሚተረጎመው የኤሌክትሮኒክስ ግዥ አጠቃቀም የህዝብ ጨረታዎችን በማመቻቸት ቅልጥፍናን ከማሳደግ ባሻገር ፉክክርን በመጨመር እና አስተዳደራዊ ሸክሞችን በመቀነስ የመንግስት ባለስልጣናትን በመያዝ ግልፅነትን ማሻሻል ያስችላል።

የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የመንግስት ግዥ በአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዝ ሲሆን ይህም ለሀገር ልማትና እድገት ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለው ይነገራል። የኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ስርዓት (egp) ጊዜና ቦታ ሳይገድቡት መረጃንና ገበያን ለሁሉም እኩል ተደራሽ የሚያደርግ ነው። በተለይ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ እያደገና እየዘመነ መምጣቱን ተከትሎ ፣ የግዥ ስርዓቱን የተቀላጠፈና ከሙስና የፀዳ እንዲሆን በማድረግ ጥቅሙ የጎላ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። ዛሬ ላይ ኢኮኖሚያቸው አድጓል ፣ በኢንዱስትሪ በልጽገዋል የሚባሉ አገራት ዘመን ወለዱን ኢንተርኔት በመጠቀምአሰራራቸውንየተቀላጠፈና ተደራሽ ማድረግ ችለዋል። ከዚያም አለፍ ሲል በመንግስት መስሪያ ቤቶች በየአመቱ የሚያካሂዱትን የምርት ፣ አገልግሎት እና ኮንስልታንሲ አገልግሎት ግዥ ለማካሄድ ከወረቀት (ማኑዋል) አሰራር በመውጣት ወደ ዲጂታል አሰራር መግባታቸው የመንግስትን ወጪ በእጅጉ እንዲቀንሱ አስችሏቸዋል ።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዓለም ዙሪያ የመንግስት ተቋማት የሚፈፅሙት የማንዋል ግዥ ከአጠቃላይ በጀት ከ60 እስከ 70 በመቶ ድርሻ ይይዛል። ይህም ማለት የጥቅል አመታዊ ምርት እስከ 14 በመቶ ብክነት አለ እንደማለት ነው። ከዚህ መረዳት የምንችለው የመንግስት ተቋማት ከፍተኛ ግዥ ለሙስናና ምዝበራ የተጋለጠ መሆኑን ነው። በመሆኑም ከፍተኛ በጀት የሚጠይቀውን ይህንን የመንግስት ግዥ አሰራር ለተለያዩ ሙስናና ምዝበራ ተጋልጦ ቀይቷል። ይህም ሊሆን የቻለው ደግሞ አሰራሩ ቴክኖሎጂ የራቀውና በማንዋል ( በወረቀት) የሚሰራ መሆኑ ዋነኛ ምክንያት ነው። ይህንን ቀድመው የተረዱ የበለፀጉ አገራት ታዲያ ኢንተርኔትን በመጠቀም የግዢ ሰርዓታቸውን ኤሌክትሮኒክስ መር ካደረጉ ከሰስት እና አራት አስርታት በላይ ተቆጥረዋል። ሀገራቱ የአሌክትሮኒክስ የግዢ ስርዓትን መከተላቸው አሰራራቸውን ከማቀላጠፉም ባለይ ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማስፈን እንደቻሉ ይነገራል።

### የሀገራት ተሞክሮ ምን ያሳየናል

የኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ስርዓትን የተገበሩ አገራት ተጠቃሚ መሆናቸውን የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከወረቀት ንክኪ በመላቀቅ የኤሌክትሮኒክስ ስርዓትን ተከትለው የንግድ ስራቸውን የሚሰሩ አገራት ቀደም ሲል ይባክን የነበረውን ከ5 እስከ 25 በመቶ ማዳን መቻላቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ። ከእኛ ቀደም ብለው የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሰርዓትን የተከተሉ አገራት በቢሊየን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ከብክነት ማዳናቸውን የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት ጥናት ያሳያል። ደቡብ ኮሪያን ብንወስድ ቀደም ሲል በማኑዋል የግዥ ስርዓት ይባክን የነበረን 8 ቢሊየን ዶላር ማዳን ችላለች። በተመሳሳይ ባንግላዴሽ የተባለቸው ሀገር ለኢትዮጵያ ጥሩ ማሳያ ልትሆን ትችላለች። ይህች ሀገር በግዥ ስርዓቱ ውስጥ በሙስና ተያያዥ ምክንያቶች መንግስታቸው ያጣው የነበረውን 1 ቢሊየን ዶላር ማዳን እንደቻሉ ይነገራል።

### የተደቀኑ ፈተናዎች

በኢትዮጵያ የግዢ ስርዓት ከፍተኛ ሙስና ያለበት ዘርፍ እንደሆነ ይታወቃል። በተለይ የመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚደረጉ ጨረታዎች ፍታሃዊነት የሌለባቸው በዘመድ ፣ በሃይማኖትና በዘር የሚካሄዱ እንደነበር የሚናገሩት የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳ ናቸው። መንግስትን ከብዝበዛና ከሙስና በመታደግና የሚባክን ወጭን በመቆጠብ ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛል። ኢትዮጵያም ቀደም ሲል ለበርካታ ዘመናት ሲሰራበት የነበረውን የማንዋል ( ወረቀት ) የግዥ ሰርዓትን በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት እንዲሆን የማድረግ ስራ አዋጅ ወጥቶለት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ስድስት አመታት ቢቆጠሩም ፣ ወደ ስራ የተገባው በግዕዝ አቆጣጠር በ2014 ላይ ነው።

ግንዛቤ ያስፋልኛል በሚል ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው የንግድ እና ሲቪል ማህበራት ተወካዮች ጋር transform public procurement through digitization; Electronic government procurement ( e-gp) for association and cso's በሚል የግንዛቤ ማስፊያ መርሃ ግብር አካሂዶ ነበር። የባለስልጣኑ ዋና ዳሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳ እንዳሉት ይህንን ስርዓት መተግበር መጀመራችን ቀደም ሲል በማኑዋል ስንሰራ ይገጥም የነበረውን አሰራር ችግር ሙሉ በሙሉ የሚያስቀር ነው ብለዋል።

አሁን ላይ ከሞላ ጎደል በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ዘንድ አሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ስርዓት እየተተገበረ ቢገኝም አንዳንድ ተቋማት ዛሬም ድረስ ከማንዋል አሰራር ሳለመውጣት ፍቃደኛ አለመሆናቸውን ያነሳሉ። በእርግጥ አዲስ አሰራር እስኪለመድ ድረስ ፈተና ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ቢሆንም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱን የገጠመው ግን ከዚህ የተለየ ነው ይላሉ።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ፈተና የሆነበት መጀመሪያ አካባቢ ላይ ከተለመደው አሰራር ሳለመውጣት የመፈለግ ዋነኛው ነው። ምክንያቱ ደግሞ መንግስትን ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርጉ አሰራሮች የሚያስቀር በመሆኑ በግዥ ሰራተኞች ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ ነው ይላሉ። ይሁንና የሲስተሙ አለመስራት ሳይሆን እነሱ እንዳይሰራ አድርገው በመቆለፋቸው መሆኑ ተደረሰበት። ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት እንዲገቡ ከተደረጉ ሰባ-አራት የፌደራል መንግስት ተቋማት መካከል አንዳንዶቹ ሳለመቀበል ማንገራገራቸውን ጠቅሰዋል።

በፍፁም ከመንግስት ተቋማት ፈተና ይገጥመናል ብለን አልጠበቅንም ፤ ስጋታችን የነበረው የንግድ ማህበረሰብ ላይቀበለው ይችላል የሚል ነበር ፤ የሆነው ግን በተቃራኒው ነው ብለዋል አቶ ሃጂ። የንግዱ ማህበረሰብ እንኳን ወደዚህ ስርዓት መጣችሁ ለሁሉም ነጋዴ እኩል የመወዳደሪያ መድረክ የሚፈጥር ነው። አንዳንድ ሰራተኞች የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሰርዓቱን በመቃወም ስራቸውን እስከመልቀቅ የደረሱበት ሁኔታም እንዳለ ገልፀዋል። ሆኖም በፍፁም ከመንግስት ተቋማት ፈተና ይገጥመናል ብለን አልጠበቅንም ነበር ፤ ስጋታችን የነበረው የንግድ ማህበረሰብ ላይቀበለው ይችላል የሚል እንደነበር ጠቅሰው ፤ የሆነው ከጠበቅነው በተቃራኒ ነው ብለዋል።

በሀገሪቱ ከ30 ሺ በላይ አቅራቢዎች ( ነጋዴ ) እንዳለ ይታመናል። ይሁንና የተመዘገበው ነጋዴ 13 ሺ ብቻ ነው ፤ የንግድ ማህበራት ሁሉም አቅራቢዎች እንዲመዘገቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰሩ እንደሚገባ በውይይት መድረኩ ላይ ተገልጧል።

### የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ጠቀሜታ

ቀደም ሲል የነበረው የማኑዋል ግዥ አሰራር ግልጽነት ያልነበረበት ፣ ሙስና እና ተያያዥ ችግሮች የነበሩበት በመሆኑ ፍትሃዊ በሆነ የንግድ ውድድር ተወዳድሮ ማሸነፍ አይቻልም ነበር ። ምክንያቱ ደግሞ ዘር ፣ሃይማኖት እና ብሄርን የተላበሰ ግዥ ይካሄድ ስለነበረ ነው። ይሄም አሰራር ግልፅነት የጎደለው ፣ ለሙስና የተጋለጠ ከማድረግ ባለፈ መንግስትን ለከፍተኛ ምዝበራ የዳረገና የሀገርን ኢኮኖሚ የሚጎዳ አሰራር ነበር። የኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ሰርዓት ግን የተጠቀሱትን ችግር በመቅረፍ ነጋዴው እኩል ተወዳዳሪ እንዲሆን ከማድረግ በዘለለ መንግስትንም ከምዝበራ የሚታደግ መሆኑን አቶ ሃጂ ጠቅሰዋል።

ያደጉ አገራት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሰርዓትን ተግባራዊ ማድረጋቸው ይባክን የነበረውን ወጪ እስከ 25 በመቶ ማዳን ችለዋል። ኢትዮጵያ ይህንን ኢንተርኔት መር የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ስታውል በትንሹ አምስት በመቶ ወጪ ቢቀንስ 40 ቢሊየን ብር ከብክነት መካካል ይቻላል ተብሎ ይገመታል። ይህም የአንድ ክልል በጀት እንደ ማለት ነው። የገንዘብ ብክነት የሚቀንሰው

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ ተግባራዊ ማድረግ ለንግድና ኢንቨስትመንት ማደግ ወሳኝ ድርሻ አለው

ከ ገጽ 1 የዞረ

ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በዚሁ ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ ወይንም (RBC) ዙሪያ ላይ ያተኮረ ስልጠና ከተለያዩ ዘርፎች ለተውጣጡ ባልድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫና ስልጠናና የልምድ መለዋወጫ መድረክ አካሂዶ ነበር:: በስልጠናው መክፍቻ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተ ማርያም ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ ለአንድ ኩባንያ ወይንም ለጥቂት ድርጅቶች ብቻ የሚተው አለመሆኑን ነው የገለፁት::

ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ሥራ የዚህኛው ኩባንያ ወይንም የዚያኛው ኩባንያ ኃላፊነት ነው የሚባልበት ጊዜ አብቅታል::

ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ አሁን ላይ በዓለም ዙሪያ ኮዶች ፣ ደረጃዎችን እና መመሪያዎችን ይከተላል:: ከእነዚህ ደንብና መመሪያዎች መካካል አንዳንዶቹ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት ( OECD) በብዝሃ ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖች መመሪያዎች ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: በተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ መርህ መኖሩን የተናገሩት ዋና ጸሀፊው የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ፣ ፀረ-ሙስና ፣ የአከባቢ ጥበቃ እንደዚሁም ለንግድና ሰበዓዊ መብቶች በተባበሩት መንግስታት መመሪያ ውስጥ ተዘርዝረው የሚገኙ መርሆች ናቸው በማለት ባደረጉት ንግግር ገለጸዋል::

የንግድ ድርጅቶች ከተቀጣሪ ሰራተኞች መብት ጀምሮ እስከ አከባቢ አየር እንክብካቤ ህግን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ የሚጠይቀው ዓለም አቀፍ መርህ በአብዛኞቹ ኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች ዘንድ ብዙም የሚታወቅ አይደለም:: ነገር ግን አሁን አሁን በዓለም አቀፍ ገበያ ገብቶ ተወዳዳሪ ለመሆን እና ዘመናዊ የንግድ መርህ መከተል የግድ የሚባልበት ጊዜ ላይ ደርስናል በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ገበያን ለውጭ ገቢያ ክፍት ከማድረግ አንፃር ኃላፊነት የሚሰማው ንግድ መተግበር መቻል አስፈላጊ መሆኑን ዋና ጸሀፊው አክለው ገልፀዋል::

አሁን መነጋገር የሚያስደስተውና በጣም አስፈላጊው ነገር ፣ሁሉም ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስነ ምግባር እና ፖሊሲዎች እና ደንቦች መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ማጉላት የምፈልጋቸው ሁለት ነገሮች አሉ ያሉት አቶ ሺበሺ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን እየከፈተች መሆኑን አሁን የኢኮኖሚ ተዋናዮቿን ከሌላው አለም ጋር ለማዋሃድ እየሞከረም ነው:: ይህ እንደምታውቁት ብዙ እድሎች ይዞ ይመጣል ነገር ግን ብዙ ፈተናም አለው:: ስለዚህ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ እየሠራን ባለው ሁኔታ፣ ኃላፊነት የሚሰማው የቢዝነስ ሥነ ምግባር ላይ የሚደረገው ውይይት በእርግጥም በሂደት ላይ ላለው እና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለውድድር ክፍት ለማድረግ እየተደረገ ላለው ዝግጅት ጠቃሚ ይመስለኛል:: ስለዚህ የንግድ እና የገበያ መከፈት የተለያዩ ዘርፎችን እና የተለያዩ ኢኮኖሚዎችን በተለየያ መንገድ መንካቱ አይቀሬ እንደሆነ ዋና ጸሀፊው በዝርዝር አስረድተዋል::

ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራ ለኩባንያ አመራር በጣም ወሳኝ የሆነ ኃላፊነትን ለሁሉም ሰራተኛ በየደረጃው የሚሰጥ ፣ ማለትም የድርጅቱን ባለቤት ፣ ስራተኞች በየዘርፋቸው ሃላፊነትን የሚሰጥ ከስጋት የፀዳ ለሁሉም ሰው ምቹ የሆነና ጤነኛ የንግድ ከባቢን ለመፍጠር የሚረዳ ጥበብ መሆኑን ይነገርለታል:: የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራትም ይህንን የንግድ ስነ ምግባር የታከለበት ኃላፊነት ይበልጥ ለማስፋፋት እየሰራ መሆኑን አቶ ሺበሺ ተናግረዋል::

ንግድ ምክር ቤታችን ኃላፊነት የሚሰማው ንግድ መፈጠር ላይ እየሰራ ይገኛል:: ብዙ ነገሮች አሉን ፣ እኔ እንደማስበው ኃላፊነት ያለበት ንግድ በኢትዮጵያ በደንብ ብናስተዋውቅ ጥራት ያላቸው ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ ይረዳናል ፣ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ጥሩ ካፒታል ያላቸውን መሳብ ተችሏል ስራ ፈጥረዋል ፣ ሃብት አምጥተዋል እንዲሁም በፈጠሩት ኢንቨስትመንት ለዜጎች ገቢ ፈጥረዋል ያንን እንወዳለን:: ነገር ግን ጥራት ያለውን ኢንቨስትመንት ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ መዋለ ንዋዮችን (ኢንቨስትመንትን) በድጋሚ መቃኘት ያስፈልጋል ብለዋል ዋና ጸሀፊው::

ኃላፊነት የሚሰማው የንግድ ስራን እውን ማድረግ የኩባንያዎችን በሰነ-ምግባር የታነፀ ንግድ እንዲያካሂዱ ያደርጋል:: ይህውም ከደንበኞች የሚመጣን ቅሬታዎችን ተቀብሎ ማስተናገድና ማስተካከያ ማድረግን ይጨምራል:: ይህ ደግሞ ለዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ብቻ የተተወ አይደለም:: ትናንሽ የንግድ ድርጅቶችም ይህንን ኃላፊነት ያለበት የንግድ ሰነ ምግባርን ቢተገብሩ ለድርጅታቸው እድገትና ዘላቂ መሆን እንደሚያግዝ ምንም ጥርጥር የለውም:: አቶ ሺበሺ ምክር ቤታቸው በሃላፊነት የሚሰራ ቢዝነስ የምክር ቤቱ የፓሊሲ አድቮኬሲ አካል መሆኑን ጠቅሰዋል::

ለንግድ ምክር ቤታችን ኃላፊነት የተሞላበት የንግድ ሥራ የፖሊሲ አድቮኬሲ አንዱ ተግባር ነው:: ሰለዚህ ኃላፊነት ያለው የንግድ ሥራ ለመተግበር ኩባንያዎች እንዴት መደገፍና የንግድ ስራዎችን ማበረታታት አለባቸው የሚለው ላይ የበለጠ ስራ መስራት እንፈልጋለን:: ስለዚህ፣ ኩባንያዎች ኃላፊነት በተሞላበት የንግድ ሥራ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የፖሊሲ ጉዳይ በማድረግ ከመንግስት እና ፖሊሲ አውጪዎች ጋር ለወደፊቱ ለመስራት እንሞክራለን::

ሁለተኛው ጠቃሚ ነገር በተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ስምምነት ላይ ሥራ የጀመርነው መሆኑ ነው፤ እኛ የተባበሩት መንግስታት የልማት ማዕከል (UNDC) የምስራቅ አፍሪካ አውታረመረብ አካል ነን ይሁንና ግን በኢትዮጵያ ውስጥ አገራዊ አውታረመረብ ለመክፈት እና ማቋቋም እንፈልጋለን:: ከ COVID በፊት የጀመርነው ሥራ በእንናተ ተሳትፎ ተሳትፎ ይቀጥላል ፣ ስራው ከ COVID በፊት የጀመርነው የነበረ ቢሆንም በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ተቋርጦ የነበረ ሲሆን አሁን ዳግም መልሶ በማቋቋም በአዲስ መልክ ልንጀምር ነው በማለት የምክር ቤታቸውን የወደፊት አቅጣጫ ተናግረዋል::

ከዳኒሽ ኢንዱስትሪ ፌደሬሽን ጋር በመተባበር በተዘጋጀውና በሪስፖንሲብል ቢዝነስ ኮንዳክት ላይ ያተኮረው ስልጠና ከተለያዩ ንግድ ዘርፎች የተውጣጡ የንግድ ድርጅት አመራሮች የተሳተፉበት ሲሆን ስልጠናውን የሰጡት ከዳኒሽ ቸርች ኤይድ የመጡት ሚስ አማንዳ ራያን በሃላፊነት የሚሰራ ቢዝነስ ዓለም አቀፍና ብሄራዊ መመሪያዎችንና ደረጃዎችን ጠብቆ መስራት አለበት ብለዋል::

RBC ኃላፊነት ያለው የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ቃሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሰብአዊ መብቶች ፣በሠራተኛ መብት ፣ በፀረ-ሙስና እና በአከባቢ ፅበቃ ዙርያ ትኩረቱን እንደሚያደርግ ገልጸዋል:: ስለዚህ እኛ የምንችለውን ያህል ፍላጎታችንን ለማገዝ የተቀየሰ ማዕቀፍ ነው:: በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ በተደረገው ስምምነት ወይም ከዓለም አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት ጋር በተደረገው ስምምነት ብሔራዊ ሕግን እና ዓለም አቀፍ ህጎችን ስንመለከት ከዚህ ዓይነት ማዕቀፍ ጋር አብረው ሲሰሩ ቆይተዋል::

እኛ ለማድረግ እየሞከርን ያለነው ለንግድ እና ለሲቪል ማህበራት በካባቢ ተፅዕኖ ላይ የበለጠ ትኩረት በማድረግ እንዲወያዩ ለመርዳት ነው:: የንግድ ጉዳይን የማመጣጠን ይህ ገጽታ ሊኖረን ይገባል:: በተለይ አሁን ያለው ማሕበራዊ ተጽእኖ በአካባቢ ላይ ያለው ተጽእኖ ሁላችንንም በተለይም በጣም ተጋላጭ የሆነውን ህዝብ እየመታ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን እርዳታ የምንጀምረው ለዚህ ነው በማለት ተናግረዋል::

ኃላፊነት ያለበት የንግድ ሥራ በዓለም አቀፍ መርህ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያነሱት ደግሞ በዳኒሽ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ አማካሪ የሆኑት ሚስተር ስቨን ፔደርሰን በበኩላቸው ኃላፊነት ያለበት የንግድ ሥራ ከጠቅላላው የእሴት ሰንሰለት ጋር አብረው የሚሰሩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው::

ስለዚህ እኛ የምንሰራው ከኩባንያዎች ጋር በቀጥታ ሊሰሩ ከሚችሉት ጋር ብቻ ሳይሆን ከአቅራቢዎች ፣ ከገበሬዎች ፣ ጋር እንዴት እንደሚሰሩ ጭምር ነው:: ስለዚህ በአካባቢዎች ያሉ ባለድርሻ አካላት እና አጋሮች አጠቃላይ እይታን ለማግኘት እንሞክራለን ፣ ይህም አካባቢን ፣ የሥራ ሁኔታን ለማሻሻል፣ ሙስናን መዋጋት መቻል ኩባንያው ቢዝነስ መስራት ብቻ አይደለም አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ መላው የንግድ ማህበረሰብ በንግድ ዙሪያ የሚሰሩት ስራ ስኬታማ እንዲሆን ያስችላል በማለት ተናግረዋል::

በዚህ የልምድ ልውውጥ መድረክ ላይ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት የሆኑ የንግድ ተቋማት ልምድና ተሞክሮአቸውን አካፍለዋ:: በተለይም ደግሞ በግብርና ማቀነባበር የቢዝነስ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች በአር ቢሲ አተገባበር ላይ እያጋጠማቸው ስላለው ተግዳሮት እና ምርጥ ተሞክሮን አካፍለዋል::

# አንድ አፍታ ከስራ ፈጣሪዎች ጋር

**« የምንሰራው ስራ በጭፍንና ሌላ ሰው ሰርቶት ስለተሳካለት መሆን የለበትም... »**



**በከፍያለው ዋሲሁን**

የባሮክ ኢንቴርየር እና ኢቨንት የተሰኝ ኩባንያ መስራችና ባለቤት ናቸው:: ይህንን ስራ ከመጀመራቸው በፊት ቀደም ሲል ይሰሩበት የነበረው መስሪያ ቤታቸውን እንደ ኮሌጅ ይመስሉታል:: ብዙ ትምህርትና የስራ ልምድ እንዳገኙበት ፤ አብረዋቸው ይሰሩ የነበሩ ባልደረቦቻቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነትም እንደ ቤተሰብ እንደነበር ያስታውሳሉ:: ፍቅር የሞላበት ቦታ እንደነበር ይገልጻሉ:: የነበረው የስራ ከባቢ የማይሰለች ነበር:: የነበረው የስራ ጫናም የዚያን ያህል ከመሆኑም በላይ የራስን ነገር እንዳታስታውስ የሚያደርግ ፤ ፋታ የማይሰጥ ቦታ ነበር:: ያ ዛሬ ለደረስኩበት እና የራሴን ድርጅት እንድመራ ትልቅ ተሞክሮ ሰጥቶኛል ይላሉ:: ምንም እንኳን ቤት የማሳመር ፤ ቢሮን የማስተካከል በፍቅር ብትወደውም ፤ እንዲህ እንጀራ ይሆናል ብላ አስባ አታውቅም ነበር:: ለእረፍት በሄደችበት ቦታ ከህልሟ ጋር ተገናኘች:: ያቺ የመጀመሪያ ስራዋ በአመት የማታገኘውን ገንዘብ በ20 ቀን አስገኘላት:: ይህም ስራ ከተቀጣሪነት ወደ ቀጣሪነት አሸጋገራት::

**አዲስ ቻምበር፡-** ኢንቴርየር ዲዛይነር ማለት ምን ማለት ነው ከሚለው እንጀምር

**ወ/ሮ ሰሎሜ፡-** ኢንቲርየር ዲዛይን ማለት ልክ የአንድ የሙዚቃ ኦርኬስራ ኮንዳክተር እንደማለት ነው:: ኢንቲርየር ዲዛይነሩ ያሰበውን ወይንም ዲዛይን ያደርገውን ነገር ሌሎች ባለሙያዎች (ፕሮፌሽናሎች) መምራት እና ማሰራት ነው:: ለምሳሌ መጋረጃውን የሚሰራው ሌላ ነው:: ነገር ግን መጋራጃው ምን አይነት ጨርቅ ምን አይነት ቀለም የሚለውን የሚወስነው ኢንቲርየር ዲዛይነሩ ነው:: ምንጣፉ ወይንም የመሬት ወለል ምን ይሁን የሚለውን የሚወስነው እሱ ነው:: መብራቶቹ ፣ ሶኬቱ ፣ ማብሪያ ማጥፊው የት ጋር ይሁን የሚለውን ኢንቴርየር ዲዛይነሩ ነው የሚወስነው:: ሶፋው የት ጋር ይሁን ቴሌቬዥኑ የት ጋር ቢሆን ነው ለዓይን የሚመቸው የሚለውን ስራ ይሰራል:: እነዚህን ስራዎች ሁሉ የሚሰሩ የተለያዩ ባለሙያዎች አሉ:: አናጢው ይሁን የጅብሰም ሰራተኛው መጋረጃ ሰፊው የእንጨት ስራ የሚሰራው ሃሳቡ ወረቀት ላይ ሰፍሮ ፣ሌሎች ባለሙያዎች አንብበው ተግባብተው በመስራት ውጤት የሚያመጡበት ነው:: ኢንቲርየር ዲዛይንና ዲኮር ልዩነት አለው:: ምክንያቱም ሁሉም የሚያስበው ማስዋብ በሚለው ነው:: ኢንቴርየር ዲዛይን ማሰዋብ ብቻ አይደለም:: የሚመች ነው ወይ የሚለውን ጨምሮ የሚሰራ ነው::

**አዲስ ቻምበር** - ከዚያ በፊት ግን የኢንቴርየር ዲዛይን ሙያው ነበረሽ ?

**ወ/ሮ ሰሎሜ** - አዎ መሰረታዊ ትምህርቱ ነበረኝ:: ህንድ አገር ውስጥ ነበር የምኖረውና ፤ ህንድ አገር ቦምቤይ ዩንቨርስቲ ነበር የምማረው:: ነገር ግን የኢንቴርየር ዲዛይንን ሰለምወደው ብቻ የሆቢ ክላሶች ብለው የሚሰጧቸው ትንንሽ ኮርሶች ነበሩ:: ከነዚያ መካከል አንዷን ወሰጄ ነበር:: በልጅኔቴም ቤት ውስጥ እቃ ማስተካከል ፣ አንድ ላይ የሚሄዱ ቀለሞች ምንድን ናቸው የሚሉ ነገሮች ባጣም ያስደስቱኝ ነበር::

**አዲስ ቻምበር** : - አሁን ላይ የምትሰሪውን ስራ የጀመርሽው በአጋጣሚ ነው ወይንስ የህልምሽ ስራ ነበር ሰለዚህ ንገሪኝ

**ወ/ሮ ሰሎሜ** :- እውነት ለመናገር ተቀጥሬ በምሰራበት ጊዜ ባክግራውንዴ ማለቴ ወላጆቼም ሆኑ ተቀጣሪ የመንግስት ሰራተኞች ነበሩ:: በአካባቢዬ ሆነ በዙሪያ በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ የማውቀው ሰው ስላልነበር ስለ ንግድ ስራ የማውቀው ነገር አልነበረም:: ነጋዴነትን እኔም ሆንኩ ሌሎች የቤተሰቡ አባል የምናስበው አልነበረም:: የምንባለው የነበረው ተምራችሁ ስራ ያዙ ፤ ተቀጠሩ ፤ ደሞዝ እንድታገኙ ጥሩ ትምህርት ተማሩ የሚል አይነት ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደኩት የንግድን ነገር አላውቀውም ነበር ማለት ይቻላል:: ነገር ግን ስራ ቦታየ ላይ ማለትም ይህንን ስራ ከመጀመሬ በፊት እሰራበት የነበረው ተቋም የተለያዩ ሁነቶችን ( ኢቨንቶችን) ማዘጋጀት አንዱ ስራየ ነበር:: በጣም ብዙ ወርክሾፖች ፣ ኮንፈረንሶች ፣ ሰብሰባዎች ይዘጋጃሉ:: እነዚያን ሁሉ ስራዎች የሚሰራው የእኔ ክፍል ነበር:: አንድ ኤቨንት ሲዘጋጅ ማነው የሚጠራው ፣ በምንና እና እንዴት ነው የሚጠራው ሁነቱ የት ቦታ ነው የሚሆነው ቦታው ላይ ምን ምን ያስፈልጋል ፣ ምግብና መጠጥ ይኖራል ወይ የሚለውን ስራ ሁሉ ስለምንሰራ ለእኔ እንደ ሁነት አዘጋጅ (ኢቨንት ኦርጋናይዘር) ጥሩ የመለማመጃ ቦታ ነበር:: የኢንቴርየር ዲዛይንም ቢሆን ቤቴም ውስጥ ይሁን በአካበቢያ ያሉ ሰዎች ምን ምን መሰራት እንዳለብኝ ያውቃሉ ፣ ቤቴን ያደንቃሉ ፣ ቢሮየን ያደንቃሉ:: ሰለዚህ የሆነ ነገር ማድረግ ሲፈልጉ የተለያየ አይነት እርዳታ ይጠይቁኛል ፤ያማክሩኛል:: ገንዘብ ተከፍሎኝ ባልሰራበትም ያንን ነገር እንደምችለው አውቃለሁ:: ከምንም በላይ ደግሞ እሱን መስራት ያስደስተኝ ነበር:: ነገር ግን እንጀራ እበላበታለሁ ብዬ የማስበው ስራ ግን አልነበረም:: ከተማችን ውስጥ አሁን ላይ በኢንቴርየር ዲዛይን የተሰራ የሚል ነገር ስሰማ ያ በራስ መተማመኔን እየጨመረው መጣ:: እኔ ይህንን ስራ ብሰራው ለካ የገቢ ምንጭ ይሆናል ብየ እንዳስብ አደረገኝ:: ከእሱ የበለጠ ደግሞ የሆነ እድሜ ላይ ስደርስ አለቃ አልፈልግም እል ነበር የራሴ አለቃ መሆን እፍልጋለሁ የሆነ እድሜ ላይ እል ነበር ህልሜን ወደ እውነት የሚቀየሩ አጋጣሚዎች ተገጣጥመው ወደ ራሴ ስራ ገባሁ::

**አዲስ ቻምበር** :- ወፍራም የሚባል ደሞዝ ተከፋይ ነበርሽና ይህንን ደሞዝ ትተሽ ወደዚህ ስራ እንድትገቢ ያደረገሽ አጋጣሚ ምን ነበር

**ወ/ሮ ሰሎሜ** ለእረፍት ከሄድንበት ቦታ ነው ከሰውየው ጋር የተገናኘነው:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች በቢዝነስ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ነበሩ ፤ ያኔ እነሱ ስለ ቢዝነስ ሲያወሩ እኔ ከእነሱ ጋር ነበርኩኝ እንጅ ምንም ነገር ውስጥ አልነበርኩም:: ለመዝናናት ከኢትዮጵያ ውጭ ነበርና ሰውየው ቢሯቸው ወሰዱን ፤ ትልቅ ሀብት ያላቸው ሰው ናቸው:: ነገር ግን ቢሯቸውን ሳይ በጣም ነበር የገረመኝ ፤ ምስቅልቅሉ የወጣ ነበር ፤ ሻይ የጋበዙን በፔርሙዝ ነው:: ጓደኞቼ እና ባለሃብቱ ሰለቢዝነስ እያወሩ እኔ ሰለቢዝነስ ሰለማላውቅ ቢሮውን ነበር የማየው ፤ አለማወቅ ብቻ አይደለም ፤ ፍላጎቱም ስላልነበረኝ ነው በእርግጥ:: የእነሱን ውይይት ትቼ ከፍሉን በአይኖቼ እያማተርኩኝ ፤ ይህ ክፍል እንዴት ፤ እንዴት ቢሆን የተሸለና ሳቢ ገፅታ ይኖረዋል እያልኩኝ አውጠንጥን ነበር:: ከእነሱ ንግግር ውጭ መሆኔን አይተው አሰለቸንስ አይደል የራሳችንን ወሬ እያወራን ሲሉኝ:: አይ እኔ በቀጣይ ጊዜ የእርሰዎን ቢሮ እንዴት ማስተካከል አለብኝ እያልኩ ነው እያስብኩ ያለሁት አልኳቸው:: ይህንን ማድረግ ትቺያለሽ ብለው ሲጠይቁኝ ፤ አዎ አልኳቸው:: እነሱ እዚያው ቁጭ ብለው አዲስ የጨረሱትን ሆቴል እንዳይ እኔን በሹፌር ላኩኝ:: የተገነባውን ሆቴል ሳይ ደስ አለኝ:: ምክንያቱም ገና የህንፃው አፅም ( ስኬሌተን ) ላይ መሆኑ በጣም ደስ አለኝ:: ምክንያቱም ኢንቴሬየር ዲዛይን የሚጠይቀው ስራ ፤ እኔም ሙሉ ስራ ሰራሁ ብየ የምለው መሀል ገብቼ ቀለም ቀብቼ፣ ቆንጆ ፍሬሞችን አስቀምጬ ሳይሆን ከመጀመርያው የኔ አሻራ አለውና በጣም ደስ ብሎኝ ነው ስራቸውን የተቀበልኩት:: አጋጣሚው ይህን ይመስል ነበር::

**አዲስ ቻምበር** - የቅጥር ስራውን ስትለቂ ባይሳካልኝስ ምን ይውጠኛል የሚል ነገር አልነበረም?

**ወ/ሮ ሰሎሜ** - ምንም ጊዜ ስራ አላገኝም ብየ ተጠራጥሬ አላውቅም:: ምክንያቱም የነበረኝ ባክግራውንድ ፣ የስራ ልምድ ፣ ምንጊዜም የትም ቦታ ማንም ሰው ሊቀጥረኝ እንደሚችል እምነቱ ሰለነበረኝ:: ባይሳካልኝስ የሚል ፍራቻ አልነበረኝም:: በወቅቱ የእኔ ፍራቻ የነበረው እንዳሰብኩት ጥሩ ውጤት ባይመጣስ የሚል ነበር:: ከምንም ነገር በላይ የምፈራው ውጤታማ አለመሆንን ነው:: ትልቁ ፍራቻየ አንድ ነገር ተጀምሮ በጥሩ ሁኔታ ካላለቀ ብየ ነበር እፈራ የነበረው:: ነገር ግን ያንን የመጀመሪያ ስራየን ለመስራት 20 ቀን ነው የፈጀብኝ:: ተቀጥሬ ስሰራ በዓመት የማላገኘውን ደሞዝ በ20 ቀን ያገኘሁት:: ይህም የበለጠ በራስ መተማመንን ሰጠኝ:: ከእሱ የበለጠ ደግሞ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለስኩ በሶስት ወር ውስጥ ለማስረከብ ያለምንም ከፍያ ሌላ ቢሮ የማስዋብ ስራ ሰራሁ:: በመጨረሻው ቀን ሳስረክብ ከማንም ሰው ስራውን በተመለከተ አንድም እንከን አልሰማሁም:: እሱም ሌሎች ስራዎችን እንድሰራ መሰመር ከፈተልኝ:: ከዚያ በኃላ ምንም አይነት አድቨርታይዚንግ ስራ አልሰራሁም:: እውነተኛው በር የተከፈተው በዚህ ስራየ ነው::

**አዲስ ቻምበር ፡-** የራስሽ ስራ በመፍጠር ለሌሎችም እንጀራ በር ከፍተሽል ከዚህ አንፃር የምትይን ነገር አለ

**ወ/ሮ ሰሎሜ ፡-** ስራ መፍጠር ጥሩ ነው :: የምትፈጥረው ስራ ፓሽኔት እና እውቀቱ ወይንም ክህሎት ሊኖርህና ደፋር መሆን አለብህ:: መሰል ስራ ከሚሰሩ ሰዎች ትምህርት መውሰድ መቻል አለብህ::ባሮክ ተፈጠረ ማን ነው የሚሰራው ? ሌሎችን መቅጠር አለብን:: የግድ ሰራተኞች ያስፈልጉናል:: አሁን ለምሳሌ ባሮክ ውስጥ የነበሩ ከትምህርት ቤት ኢንተርንሺፕ የመጡ ልጆች ባሮክ ውስጥ ሰርተው አሁን ወጥተው የራሳቸውን ስራ ፈጥረዋል:: የግድ ተቀጣሪ ሆነው ይቅሩ አልልም:: ሙያውን ለማስፋፋት እነዚህ ልጆች የራሳቸውን ቢዝነስ መጀመር አለባቸው:: ማንም ሰው የሚያምንበትን ስራ እኔ ይሳካልኛል ፤ እችለዋለሁ ያለውን ስራ መስራት ይችላል:: ለምሳሌ ቀደም ብየ እንደገለፅኩልህ ደሞዜን ጥየ ስገባ ምንድን ነው የምከፍለው ለቢሮ ክራይ ፣ ፕሮጀክት እስከማገኝ ድረስ ለስድስት ወር የሚሆን ገንዘብ መኖር አለበት:: ሰለዚህ ቀድመን ማሰብ አለብን:: የምንሰራው ስራ በጭፍንና ሌላ ሰው ሰርቶት ስለተሳካለት መሆን የለበትም:: በደንብ ቢዝነስ ፕላን ሰርተን አንድ አመት ምንድን ነው የማደርገው ፤ ሁለት አመት ምንድን ነው የማደርገው የሚለውን አስቀድመን ማቀድ አለብን::

**አዲስ ቻምበር ፡-** ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሊሆን አይችልምና ፈተና የሆነብሽ ምን ነበር

**ወ/ሮ ሰሎሜ ፡ -** ደሞዝ ለምደህ ወደ ግል ስራ ስትመጣ አንድ ጊዜ ጥሩ ደሞዝ ልታገኝ ትችላለህ ፤ ሌላ ፕሮጀክት እስከምታገኝ ድረስ ስራ ሳይኖርህ ቁጭ ልትል ትችላለህ:: ሰለዚህ ጥሩ ባክ አፕ ሊኖርህ ይገባል:: ለምሳሌ የቢሮ ክራይ እየከፈልክ ጥሩ ወርኪንግ ካፒታል ሳይኖርህ ለሰራተኞች መክፍል አለብህ:: እነዚህ ነገሮች ከባድ ይሆኑብሃል:: ግን ምንድንነው ችግሮች

**ወደ ገጽ 8 ዞሯል**

## እናስተዋውቃችሁ

# ከከረሜላ አዟሪነት እስከ ባለብዙ ኩባንያዎች ባለቤትነት



*** ዩቲዩብን እና ሊንክድ ኢንን ጨምሮ ከ150 በላይ በዲጂታል ፣በፋይናንስ ፣በታዳሽ ሃይል እና ሌሎች ዘርፎች አዳዲስ ቢዝነሶችን ሃሳብ ያፈለቀ፣ኩባንያዎችንም ያቋቋመ፥ አሜሪካዊው ሥራ ፈጣሪ ቢል ግሮስ

በይድቃቸው ዓለማየሁ

ስኬታማ ሰዎች ወደ መድረክ ብቅ ሲሉ በተደጋጋሚ የሚቀርብላቸው የተለመደ ጥያቄ ቢኖር “እንዴት እና በምን ሁኔታ ወደ እዚህ ቢዝነስ ውስጥ ልትገባ ቻልክ/ቻልሽ ?” የሚለው ነው። አንዳንዱ በዕቅድ፣ሌላው በድንገት በተፈጠሩ እድሎች አልያም ስገዳጅ ሁኔታዎች ፣እልፍ ሲል ደግሞ የመጣው ይምጣ ብለው ኃላፊነት ወስደው ወደ ቢዝነስ የገቡ መሆናቸውን ከትዝታቸው ዋሻ አውጥተው ይመልሳሉ።

በተለይ ወደ ቢዝነስ ዓለም ሲገባ ፍርሃት ፣ፍርሃት የሚሉ ብዙ ከባቢ ሁኔታዎች አሉ። በተለይ ወጣት እና ጀማሪዎች ነጋዴዎች በጥዋቱ የሚያስተናግዱት አበሳ አንዱ “እከስር ይሆን?” የሚለው ፍርሃት ነው። በተለይ በእኛ ተጨማባጭ ሁኔታ መነሻ ካፒታል የሚገኘው ከውርብ ዘመድ፣ወይም ሁነኛ ወዳጅ ነው። በተለይ ጀማሪ ነጋዴዎችን “በስንት መከራ ያገኘሁነትን ብድር እመልስይሆን ?” የሚለው ሥጋት በ2 እግራቸው እስኪቆሙ ድረስ ይዘውዛቸዋል።

እንዴት ጀመርከው/ጀመርሺው የሚለው ጥያቄ በንግድ ዓለም ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች የመጀሚያውን የጥዋት ፈተና በምን ብልሃት እንዳለፉት ለማወቅ የሚያጓጓ በመሆኑ ይመስላል እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች በብዛት የሚነሱት።

በቢዝነስ /በሥራ ፈጠራ ዘርፍ የተሰማሩ ተመራማሪዎች እንደሚሉት አንድ ሰው የተሳካለት ሥራ ፈጣሪ ወይም አንተርፕረነር ሊሆን የሚችለው በባቀደው የቢዝነስ ሃሳብና ሃሳቡን ተግባራዊ ማድረጊያ ገንዘብ ወሳኝ መሆናቸው አይጠረጠርም። ሆኖም ሃሳብ እና ገንዘብ ብቻ ማግኘት ብቻውን የተሳካለት የቢዝነስ ሰው እንዲሆን አያስችሉትም።

አንድ ውጤታማ ሥራ ፈጣሪ ከምንም በላይ የግል ሃብቱ ማድረግ ያለበት የሰብዕና መገለጫዎች ወይም የሚታይበት ባሕሪያት መላበስ እንዳለበት አጥኚዎች ይመክራሉ። በዚህ መሠረት በዘመናችን ከትንሽ ተነስተው አንቱ የተባሉ ስኬታማ ሥራ ፈጣሪዎች ዛሬ ለደረሱበት የስኬት ከፍታ ከገንዘብ እና ዕቅድ በተጨማሪ የራስ ተነሳሽነት (Self motivation) ፣ ፈተናዎችን ፊት ለፊት የመጋፈጥ (Risk Takers) የራስ ችሎታ መተማመንን ማዳበር(Self Confidence)፣ ከሌሎች ምላሽን (ግብረ መልስን) መፈለግ(keen to take lessons and feed backs) ከፍተኛ የሚንቀለቀልመሻት/ኃይል ፣(Zeal for aggrandizement)፣ስለወደፊቱ ማሰብ(Visionary)፣ነገሮችን የማቀናጀት ክህሎት (coordination)፣ ከገንዘብ ይልቅ እሴትን ዋጋ መስጠት (Emphasis Value addition over money)

በእርግጥ ሁሉም የተዋጣለት የቢዝነስ ሰው ከላይ የተሰዘረዘሩትን ባሕሪያት ሁሉንም ያሟላል በይባልም ከሞላ ጎደል አብዛኞቹ ይታዩበታል ይላል አውቁ አሜሪካዊው የቢዝነስ ሃሳብ አፍላቂ እና ሥራ ፈጣሪ ቢል ሮስ።

ይህ ሥኬታማ የንግድ ሰው ‘TED Stage’ በመባል በሚታወቀው የቢዝነስ፣የፖሊቲካ፣የማሕበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ አተኩሮ ዝነኞች ሃሳባቸውን ሚያቀርቡበት ዓለማቀፍ መድረክ ላይ ቀርቦ ልምዱን ሲያካፍል እንዲህ ብሎ ነበር፡ ፡ ንግድ ማለት ድርጅቱ፣አገልግሎቱ፣ምርቱ መሣሪዎቹ፣ወይም ሠራተኞች፣አልያም የኩባንያው ባለቤቶች ማለት አይደለም ። ንግድ ወይም ቢዝነስ ማለት አንድ ቢዝነስ ለመጀመር አንድ ሰው ያሰበው የሃሳብ ጽንስ ማለት ነው፡ ፡ አንድ ሰው አንድ ቢዝነስ ለመጀመር ባሰበበት ቅፅበት በቃ የንግድ ተጀመረ ማለት ነው ብሎ ያምናል። ታዲያ ያንን አንድ ጊዜ ብልጭ ያለ የንግድ ሃሳብ እንደ ኃይማኖት ያህል ጥብቅ አድርጎ መያዝ እና ዘወትር ማሰላሰል ይጠይቃል ይላል ሚ/ር ግሮስ።

ቢዝነስ ሁልጊዜ ማቀድ ፣ማለም፣ደጉንም ክፉውም እንዳመጣጡ መመለስ ይኖርበታል። በተለይ ከደንበኞች የሚመጣ አስደንጋጭ ወይም አሳዛኝ ግብረመልሶች ለአንድ ነጋዴ ትልቁ የእድገት መሰላል ነው ይላል።

ወደ ንግድ ዓለም በ12 አመቱ በአውቶብስ ማቆሚያ ተጠግቶ ከረሜላ እና ሌሎች ጣፋጭ ነገሮችን በማዞር እንደጀመረ የሚነገርለት የዛሬው ከበርቴ የኮሎጂ ትምህርቱን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተመርቆ እስኪወጣ ድረስ ከንግድ ሥራው አልተለየም። በዚያው በመቶዎች በተሰበሰቡበት መድረክ ላይ ከሕይወት ተሞክሮ ጨልፎ ለወጣቶች እንዲህ ብሎ ነበር።

“ ..ከሕይወት እና ከሥራ ልምዴ በመነሳት አንድ ቁምነገር ልናገር። ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች በስኬት እንዲያድጉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለሚለው ጥያቄ ከራሴ ልምድ በመነሳት አንድ ቁምነገር ልንገራችሁ” ሲል ይጀምራል፡ ፡ እኔ ቢዝነስ የጀመርኩት በ12 አመቴ ነው። የጀመርኩትም በአውቶብስ ማቆሚያ ላይ ከረሜላ በማዞር ነበር። ከዚያም 2ኛ ደረጃ ስገባ የድምፅ ማጉያ መሥራት ጀመርኩኝ፣ ከዛም ሶፍትዌሮችን ሰርቼ መሸጥ ጀመርኩኝ ፣የዛሬ 20 ግድም አንድ የንግድ ሃሳቦችን ማበልጸጊያ ማዕከል ለማቋቋም አሰብኩን ።ኢዲያል ላብ ኩባያ የሚባለው ኩባያ ያ ሃሳብ ነው። በዚያች ላብ(ቤተሙከራ እንደማለት ነው) በእነዚህ 20 አመታት ውስጥ ወደ 100 የሚጠጉ ኩባንያዎችን ለመክፈት ችለናል።

ቢል እንደሚለው ለው ውጤት ያበቁትን 5 ጠቃሚ ነጥቦችን አንስቶ አብራርቷል፡ ፡ የመጀመሪያው ሃሳብ ነው፣ ማለቴ ልንሰራ ያሰብነው ቢዝነስ ነው። በሃሳባችን የመንከፍተው ቢዝነስ ይታየናል፣እንዳስሰዋለን ነገርግን ለሌላ ሰው ማሳየት አንችልም። አሁን የምናያቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ፣አሰራሮች ሁሉ ያኔ ሃሳብ ብቻ ነበሩ ነበሩ እንደማለት ነው። ስለዚህ ሃሳብ ከሌለ በቃ ቢዝነስ የሚል ነገር የለም። ቀጥሎ፣ባለድርሻ ማወቅ እና በትብብር መስራት ነው። አንድን ቢዝነስ ስንጀምር በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ ከተለያዩ ሰዎች ፣ተቋማት ጋር እንገናኛለን፡ ፡ አንድም ለዕድገራችን አለያም ከውድቀታችን የምንማርበት ወቅት ላይ ያደርሱናል። እዚህ ላይ ከታዋቂው ቡጢኛ የማይክ ሳይሰንን አባባል ላንሳለችሁ። እርሱ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር “እኔ ሁልጊዜ ዕቅድ አወጣለሁ፣አሰባለሁ፣ ነገር ግን ደህና ቡጤ በፌቴ ላይ እስኪያርፍብኝ ድረስ አስባለሁ ። ካረፈብኝ ቡጢ ትምህርት ወስጄ እንደገና በአዲስ አቅዳለሁ” ብሎ ነበር።

የታይሰን አባባል ለአንድ ጀማሪ ነጋዴ በጣም ይቅመዋል። የኛ የነጋዴዎች ፊት የደንበኞች ቡጢ ያርፍበታል። ስለዚሀ ደንበኞቻችን የእኛ መስተዋት ናቸው። ደንበኞች ከሌሉ እኛ የለንም፣የፈለገ ጥሩ የተባለ የቢዝነስም እቅድ ቢኖረንም እቅድ ሆኖ ይቀራል። ልብ በሉ ስለሲህ ደንበኞች የቢዝነሳችን ባለድርሻዎች ናቸው። 3ኛ ቢዝነሳችን ከየት ተነስቶ በምን ያህል ጊዜ የት ለማድረስ እንደምንሰራ ጥርት ያለ ፍኖተካርታ ሊኖረን ይገባል። የስትራተጂው ግብ ትርፍ እና ደንበኞችን ቁጥር ማሳደግ ጋር አያይዞ መሳደግ መሆን አለበት። 4ኛው ፋይናንስ ነው ። ብዙ ኩባያዎች በብዙ ተበድረው ብድሩን መመለስ አቅቷቸው ሲቸገሩ ይታያል። ብድሩ ወይም የምናገኘውን መነሻ ካፒታል በእቅድ ፣በአቅማችን እና በደንበኞቻችን ፍላጎት ልክ መሆን አለበት። የመጨረሻው ጊዜ ነው። የጊዜ ጉዳይ ከደንበኞች ፍላጎት ጋር የተቆራኘ መሆን አለበት ። አንድ ጀማሪ ነጋዴ ያለኝን ምርት/አገልግሎት መቼ እና እንዴት ባለ መንገድ ወደ ገበያ ይዤ ልውጣ ብሎ አመቺ ጊዜዎችን ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ አለበት። ማለት ከተመረጠው ጊዜ በፊት ወይም በኋላ ወደ ገበያ መግባት ዋጋ ያስከፍላል። ተወዳዳሪዎቻቸን ሳይሸጡ ወይም ሸጠው ከጨረሱ በኋላ መወዳደር ኪሣራ ያመጣል። ከታች የተመለከቱት 5 ነጥቦች ለአንድ ጀማሪ ነጋዴ ወደ ስኬት ጎዳን ይመሩታ ይላል። አንድ የቢዝነስ ሃሳብ ማፍለቅ እና በሃሳብ ላይ እቅድ አውጥቶ ያንን ሃሳብ ወደ ግዑዝ ንግድ ድርጅትነት ለመቀየር አንድ ጀማሪ ነጋዴ ሕልም በመሆን አለበት። ማለትም በመጀመሪያ ምን ቢዝነስ ልጀምር እችላለሁ ብሎ ትንሽ ማሰብ ያስፈልጋል። ትልቁ ዋናው መሠረት የሃሳብ መጸነስ ሲሆን እርሱንም በሚበራ አምፖል መስሎታል። 2ኛው መነሻ ካፒታል ገንዘብ ሳይሆን ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር(ያለንን ግንኙነት ማጠናከር ፣ደንበኛ ማፍራት) ራስን ከአካባቢ ጋር ማላመድ ሲሆን እርሱንም በቢዝነስ ካርዶች ይመስለዋል። 3ኛ ው የቢዝናችን ሞዴል ነው። ይህ ማለት የመንጀምረው ንግድ የጠራ እና

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# አንድ አፍታ ከስራ ፈጣሪዎች...

ከ ገጽ 6 የዞረ

ቢገጥመኝም አንድ ጊዜ ገብቼበታለሁ ፤ ስራዩ ብየ ወሰጄዋለሁ፡፡ ይህንን የጀመርኩትን ስራ መተው አልፈልግም ፤ ማደግ እፈልጋለሁ፡፡ ሰለዚህ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት እያሳየሁ ሄጃለሁ በዚህ ሙያ ላይ ፤ ሰለዚህ መጠንከር አለብኝ፡፡ በየጊዜው የተለያዩ ፈተናዎች ይፈጠራሉ፡፡ አንዳንዴ ወጥቼ ቢሮየ በረንዳ ላይ ቁሜ ቡቲክ ከፍተው ልብስ የሚሸጡ ሰዎችን ሳይ ፤ እኔ ከወረቀት ጋር ሳልጨናነቅ ቡቲክ ከፍተው የሚኖሩ ሰዎች አሉ አይደለም እነሱ እየኖሩ ነው እኮ ብየ ያሰብኩበት ጌዜም ነበር፡፡ ይህንን ሃሳብ እንዳስብ ያደረገኝ ከሰራተኞቼ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ፤ ወይንም ከደንበኞች ጋር በነበረኝ ግንኙነት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ችግሮች መፍትሄ የሚፈልጉና የሚያልፉ ነገሮች ናቸው፡፡ ነገር ግን የገጠመኝ እያንዳንዱ ችግር የሆነ ነገር አስተምሮኝ ነው የሚያልፈው፡፡ በየጊዜው ያለማቋረጥ እራሴን አዘጋጅቼ ፤ ለሚመጡብኝ ችግሮች ሁሉ ምንድን ናቸው መፍትሄያቸው በምን አይነት መንገድ ነው ልወጣው የምችለው የሚለውን እያየሁ አልፋለሁ፡፡ ፈተናው በተለያየ መንገድ ነው የሚመጣው ፤ ብቁ ሰራተኛ ማግኘት አንዱ ነው፡፡ አንድን ትልቅ ፕሮጅክት አምነህበትና እሰራዋለሁ ብለህ እምነት ያሳደርክባቸውና አብረውህ የሚሰሩና የሚያግዙህ ሰዎች ባሰብከው ደረጃ ብቁ ሳይሆኑ ሲቀሩ ተሰፋ ያስቆርጥሃል ፤ እነዚህ በሰራዩ ላይ ያሉ ፈተናዎች ናቸው ማለት እችላለሁ፡፡

**አዲስ ቻምበር፡ -** በነገራችን ላይ ስኬታማ ነኝ ብለሽ ታሰቢያለሽ ፤ ከሆነስ የአንቺ ስኬት ምንድን ነው

**ወ/ሮ ሰሎሜ ፡-** ስኬት ብዙ ትርጉም ስላለው ፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ አተረጓጎም አለው፡፡ ስለዚህ ስኬትን በተለያየ መንገድ ልናሰቀምጠው ስለምንችል በየትኛው አይን የሚለውን ማየት አለብን፡፡ ወደ እኔ ስመጣልህ ፤ እያንዳንዱ ፕሮጀክት አንድ እናት ዘጠኝ ወር አርግዛ እንደምትወልደው ስኬት ብየ የምገልፀው የያዝኩት ፕሮጀክት አጠናቅቄ ፤ ይህው ብየ ይህንን ነበር ያለምኩት ፤ ይሀው የሚታይና የሚዳሰስ ሆኖ ለፕሮጀክቱ ባለቤት አቅርቢያለሁ ይህ ለእኔ ስኬት ነው፡፡ እያንዳንዱ የምሰራው ስራ የእኔን ስኬት ያሳየኛል፡፡ አንዱ ፕሮጀክት ላይ የተማርኩትን እያሻሻልኩ ሌላው ስራዩ ላይ ሳየው እኔን ስኬታማ ያደርገኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ባሮክ አስራ አንድ አመት እራሱን ችሎ መቆሙ አንዱ ሆኖ ፤ በሀገሪቱ ውስጥ ትልልቅ የሚባሉ ፕሮጀክቶችን ማለትም አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ቪ. አይ ፒ ተርሚናልን ያክል ለአምስት አመት የፊጀ ስራን መስራት ለእኔ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ በዚህ ሙያ እራሴን በየጊዜው እያሳደኩ መጓዝ መቻሌና ከሌሎች ኢንተርናሽናል ባለሙያዎች ጋር አንድ አይነት ቋንቋ መነጋገርና ትስስር መፍጠሬ ያ ለኔ ትልቅ ሰኬት ነው፡፡

**አዲስ ቻምበር ፡-** የኢንቴርየር ዲዛይን የመመሰረት ፍላጎቱ ነበርሽ ፤ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

**ወ/ሮ ሰሎሜ ፡-** ይህንን ስራ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ምንም አይነት ዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች ፤ የኢንቴርየር ዲዛይን ሴሚናሮች በተቻለኝ መጠን አልቀርም፡፡ ከ100 በላይ አገራት የመጡ የህንፃ ዲዛይን ባለሙያዎች (አርክቴክቶችና ኢንቴርየር ዲዛይነሮች የሚሳተፉበት ሴሚናር ላይ እሳተፋለሁ፡፡ በዚህ በምሳተፈበት ሴሚናር ያየሁት ነገር ምንድን ነው እንደ ናይጄሪያ ፤ ኬኒያ የመሳሳሉ የአፍሪካ አገሮች የኢንቴርየር ዲዛይን ማህበር አላቸው፡፡ ወደ ዓለም አቀፍ ኢንቴርየር ዲዛይን ለመግባት በግሌ አልችልም ፤ የኢትዮጵያ ኢንቴርየር ዲዛይን ማህበር ነው አባል መሆን የሚችለው፡፡ ሰለዚህ ይህ ማህበር ባለመኖሩ እኔን በግሌ አፌክት አድርጎኛል፡፡ አገር በመሆናችን አገር ውስጥ ልናገኘው የምንችለው ጥቅም እንኳን ቢቀር ፤ ዓለም አቀፍ ደረጃ ወጥተን የኢትዮጵያ ብለን እንዳንቀሳቀል ችግር ፈጥሮብናል፡፡ ስለዚህ ይህ ማህበር መቋቋም እንዳለበት ተገንዝቢያለሁ፡፡ ብዙ የሰራሁት ሆቴሎችና ቢሮዎች እና ኤርፖርት ላውንጆች ናቸው፡፡ ከደንበኞቼ የምሰማው እምነት ማጣት ነው፡፡ እዚህ አገር ምን ኢንቴርየር ዲዛይን አለ ነው የሚሉሽ፡፡ ለምንድን ነው ያ የሆነው ስንል በቀላሉ ወደዚህ ስራ ገብቶ ኢንቴርየር ዲዛይነር ነኝ ማለት ቀላል ሰለሆነ ነው፡፡ ያ ማለት ማንም ሰው መሰራት አይችልም ማለቴ አይደለም ስታንዳርድ መኖር አለበት፡፡ ለምሳሌ ጨረታ ስንወዳደር በምን መሰፍርት ነው የምንወዳደርው የሚለው ደረጃና መሰፍርት ያስፈልጋል፡፡ መንግስት እንዲያውቀን እናደርጋለን፡፡ አቅሙ ችሎታው አለን፡፡ ከኢትዮጵያም ወጥተን መስራት እንችላለን፡፡ ሰለዚህ የኢንቴርየር ዲዛይን ማህበር መኖሩ ጥቅሙ የላቀ ነው፡፡

**አዲስ ቻምበር ፡ -** ወ/ሮ ሰሎሜ ጊዜሽን ሰውተሽ ከአዲስ ቻምበር ሚዲያ ጋር ሰለነበረሽ ቆይታ እጅግ አድርጌ ነው የማመሰግንሽ፡፡

**ወ/ሮ ሰሎሜ ፡-** እኔም በኢንቴርየር ዙሪያ ምንነት እና ዘርፉ ያሉበትን ችግሮችና ቀጣይ እንደ ሀገር ልንሰራ የሚገባንን ነገር እያነሳን ሰለተጨዋወትን አዲስ ቻምበርን ሳማሰግን እወዳለሁ፡፡

# ከከረሜላ አዟሪነት...

ከ ገጽ 7 የዞረ

ግልጽ ዕቅድ ራዕይ ማበጀት ሲሆን በግራፍ ሥዕል መስሎታል፤4ኛው ገንዘብ (መነሻ ካፒታል በብር እና በሳንቲም ስዕል አመልክቶታል)፤5ኛው ጊዜ ነው፡፡ ጊዜን በጠረጴዛ ሰዓት የተወከለ ሲሆን ጊዜ ማለት ምርትና አገልግሎቴን በምን ጊዜ ይዘን ወደ ገበያ መውጣት እንዳለብን ደግሞ ደጋግሞ ማሰብነ እና መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ይኸው ነው፡፡

በተለይ የጊዜ መረጣችን ‘ላም ያልዋለበት…’ ነገር ውስጥ እንዳንገባ እና ከስረን እንዳንቀር ይረዳናል ሲል ልምዱን አካፍሏል፡፡

እኤአ በ1996 አይዲያል ላብ የተባለችውን ድርጅት ሲከፍት የነበረው ሕልም አንድ የንግድ ድርጅት መክፈት አልበረም ይላል፡፡ “እኔ የጀመርኩት አንድ የቢዝነስ ሃሳብ ማፍለቂያ የሚሆን ድርጅት ሆኖ ሰዎች የቢዝነስ ሃሳባቸውን ያለምንም ገደብ በነጻ እንዲያውጠነጥኑ እና አንድ የቢዝነስ ኩባንያ በአእሞሮአቸው ጸንሰው አንዲወልዱ ሁኔታቸውን ማመቻቸት ነው”፡፡ አይዲያል ላብ የተባለችውን ኩባንያ ለመክፈት ሲያስብ ጥሬ ዕቃው፤ግብዓቱ፤ምርቱም አዳዲስ ሃሳብ ብቻ ነበር፡፡ በዚህች ድርጅት ውስጥ ሃብታሞች ሃሳብ ይገዛሉ፤ስለታሰበው የቢዝነስ ሃሳብ በቂ የባለሙያ አዋጭነት በባለሙያ ተተንትኖ ይቀርብላቸዋል፡፡ ሃብታሞች የቢዝነስ ሃሳቦቻችንን ይገዙና ቢዝነስ ይጀምራሉ፡፡ በዚህ መንገድ ወደ 150 የሚሆኑ ኩባንያዎች ያኔ ሃሳብ ብቻ የነበሩ ዛሬ ላይ ግዙፍ ኩባንያዎች ሆነው ፤ ሠራተኞች ተቀጥረው፤ ለአገራችን ገቢ እያመነጩ ነው ይላል፡፡ እንግዲህ አንዲነበር የቢል አነሳስ፡፡ ብዙዎች ከውደቀቱ፤ከስኬቱና እና ከልምዱ አንዲማሩ የሚያካፍለው፡፡ የንግድ ሃሳብ ቸርቻሪው፤ከበርቴው፤በጎ አድራጊው እና ዛሬም ቢል ዊልያም ቲ ግሮስ ከመሠረታቸው እና በሃላፊነት ከሚመራቸው መካከል ከታች የመለከቱት ትላልቅ ኩባንያዎች ይገኙበታል፡፡




# ብቁ እና ተወዳዳሪ ኩባንያዎችን ለማፍራት....

**“ለማንኛውም አካል ስልጠና. ለአባላቶቻችንም፤አባል ላልሆኑትም ክፍት ነው።... ሁሉንም እናስተናግዳለን ”**



ለንግዱ ሕ/ሰብ ጥቅም እና መብት እንዲከበር የነጋዴው የጋራ ድምጽ የሆነው የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት ወይም አዲስ ቻምበር ለአባላቱ እና ለመላው የንግዱ ሕብረተሰብ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ ልዩ ልዩ ቢዝነስ ተኮር ስልጠናዎችን እያዘጋጀ የዘርፉን አቅም መገንባት ነው:: ይህንንም አገልግሎት የሚሰጠው በራሱ የስልጠና ማእከል ሲሆን ከዓለም ተለዋዋጭ የንድግ ሥርዓት ጋር አብሮ የሚሄዱ ቢዝነስ ተኮር ሥልጠናዎችን ይሰጣል:: ተቋሙ ወቅቱን የሚጠይቀውን ሥልጠናዎች በማዘጋጀት የነጋዴውን የቢዝነስ ክህሎት፤እውቀት በማሳደግ በዓለማቀፍ ገበያ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኝ የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቀይቷል:: ንግድ ምክር ቤቱ ስለሚሰጠው ስልጠና አስመልክቶ የተቋሙ ዳይሬክተር አቶ ደሳለኝ ደጀን ባልደረባችን ከይድነቃቸው ዓለማየሁ ጋር ቆይታ አድርገዋል::

**ንግድና ልማት:** ከሥልጠናዎች አጠቃላይ ገለጻ አንጀምር?

**አቶ ደሳለኝ:** እኛ የምንሰጣቸው ሰልጠናዎች በነጋዴው ሕብረተሰብ አጠቃላይ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: በ4 መርሐግብራት የሚካሄድ ነው:: 1ኛው መደበኛ የሆነ ስልጠናዎች ናቸው:: እነዚህ ስልጠናዎች ዝርዝር የሥልጠና ኮርሶች ተዘጋጅተው ፤ኮርሶቹ የሚሰጥባቸው የጊዜ ሠሌዳዎች እና ቡክሌቶች ተዘጋጅተውላቸው የሚሰጡ ናቸው:: 2ኛው የዚሁ አይነት ሆነው ነገር ግን ለከፍተኛ የኩባንያ አመራሮች የተዘጋጁ(Top Executive Training) ናቸው:: 3ኛው ድርጅቶች የሚጠይቁት ጥያቄዎች አሉ:: ደንበኛ-ተኮተር የሆኑ ፤ በእነርሱ ፍላጎት የሚመጡ ስልጠናዎች አሉ:: ስለዚህ እዚህ ስልጠናዎች በደንበኞች ፍላጎት የሚዘጋጁ እና የሚሰጡ ናቸው:: 4ኛው የሥልጠና አይነት በአዲስ ቻምበር ድረ-ገጽ ላይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ናቸው:: ኦንላይን የሚባለው አይነት ነው:: ይህም በZoom ቀጥታ በመሳተፍ ፤እንዲሁም የስልጠና ሰነዶችን ከድረ-ገጽ ላይ አውርደው እንዲዘጋጁ በማድረግ ሰልጠናዎችን እናካሂዳለን::

**በገቢ ና ወጪ ንግድ ሥርዓት ላይ በየጊዜው መንግሥት የሚያወጣቸውን ማሻሻሃዎች፤አዳዲስ መመሪያዎችን እያካተተን አባሎቻችን እንዲያውቋቸው እናደርጋለን። በስልጠና ዓለም ቋሚ የሚባል ነገር የለም።**

**ንግድና ልማት፡** ነጋዴው ለስልጠናው ያለው ፍላጎት ምን ይመስላል ?

**አቶ ደሳለኝ፡** ጥሩ ጥያቄ ነው... በነጋዴው በኩል ስንመለከት አሁን አሁን ለሥልጠና ያለው ዋጋ እየጨመረ መጥቷል.:: አንዳንዶቹ ተቋማትም በፖሊሲ ደረጃ የስልጠና ፓኬጅ ስላላቸው ፤አንዳንዶቹ ደግሞ ኩባንያቸው ሰራተኞቻቸውን ማሰልጠን ለሚቆጣጠሯቸው ተቋማት ሪፖርት ማድረግ ስላለባቸው ሰራተኞቻቸውን በጊዜው ያሰለጥናሉ:: በአጠቃለይ በንግዱ ሕበረተሰብ ዘንድ ሠራተኞችን ማሰልጠን ባሕል ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል:: ለምሳሌ የፋይናንስ ተቋማት በዚህ መልኩ በብዛት ሠራተኞቻቸውን ወደ እኛ ልከው ያሰለጥናሉ::

**ንግድና ልማት:** የቻምበሩ ሥልጠና ለአባላቱ ብቻ ነው ወይስ ..

**አቶ ደሳለኝ:** ለማንኛውም አካል ስልጠና ለአባላቶቻችንም፤አባል ላልሆኑትም እንዲሁም በግል ለሚጠይቁንም ስልጠና አዘጋጅተን እንሰጣለን:: ሁሉንም እናስተናግዳለን::

**ንግድና ልማት:** የኩባንያዎች ስለ ቻምበሩ ስልጠናዎች ምን ይላሉ ?

**አቶ ደሳለኝ:** ብዙዎቹ ጥሩ አስተያየት አላቸው::በአግልግሎታችን ደስተኞች እንደሆኑ ይነግሩናል:: በተጨባጭ ግን በእያንዳንዱ ስልጠና ማጠናቀቂያ ላይ ሰልጣኖችን የምናስሞላው ግብረ-መልስ አለን:: በየጊዜው ከመንሰበስበው ግብረ መልስ በመነሳት በምንሰጣቸው ስልጠና እርካታቸውን እንገመግማለን:: በዚህ አመት የደንበኞቻችን አጠቃላይ የእርካታ ዳሰሳ አድርገናል:: በዚህ መሠረት 81 በመቶ የሚሆኑት በስልጠናው እንደረኩ ምስክርነታቸውን ሰጥተውናል:: ይህ ትልቅ ቁጥር ነው፡ ነገር ግን ህልማችን 100 በመቶ ለማድረስ እየሰራን ነው::

**ንግድና ልማት፡** ዓለማቀፉ የንግድ ሥርዓት ተለዋዋጭ እና አዳዲስ ዓለማቀፍ አሰራሮችን በየጊዜው ይፈጠራሉ፤

**አቶ ደሳለኝ፡** እንግዲህ የስልጠና ማንዋሎቻችን በየጊዜው ክለሳ እና ደርጋለን:: ለማሳሌ ከዓለማቀፉ የሒሣብ ሪፖርት መስፈርት(IFRS) ፤ የአፍሪቃ ነጻ ገበያ ሥርዓት ከሚመነጩ አዳዲስ አሰራሮች፤ መመሪያዎች ወዘተ እየተከታተልን በምንሰጠው ስልጠና ውስጥ እንዲካተቱ እናደርጋለን:: ስለዚህ ነጋዴው ሕብረተሰብ ከአዳዲስ አካባቢያዊ እና ዓለማቀፍ ለውጦች መረጃ እንዲያገኝ እና ጊዜው የሚጠይቀውን ስልጠናዎች በመስጠት ከዓለም እኩል እንዲራመድ የበኩላችንን ጥረት እያደረግን ነው::

**ንግድና ልማት፡** በአገር ውስጥ ለምሳሌ በቅርቡ የካፒታል (የአክሲዮን) ገበያ እየመጣ ነው፤

**በአጠቃላይ በንግዱ ሕ/ሰብ ዘንድ ሠራተኞችን የማሰልጠን ባሕል ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል።**

**አቶ ደሳለኝ፡** በካፒታል ገበያ ላይ በቂ ዝግጅት አድርገን ስልጠናዎችን እየሰጠን ነው:: በሙያው እውቅና በገኙ ባለሙያዎች ስልጠና እየሰጠን ነው:: ሌላው ዓለማቀፍ ንግድን ላንሳ፤ በገቢና ወጪ ንግድ ሥርዓት ላይ በየጊዜው መንግሥት የሚያወጣቸውን ማሻሻያዎችን፤አዳዲስ መመሪያዎችን እያካተተን አባሎቻችን እንዲያውቋቸው እናደርጋለን:: በስልጠና ዓለም ቋሚ የሚባል ነገር የለም:: ለምሳሌ የግብር ሕግ ብንመለከት ሕጉ በየጊዜው ይሻሻላል:: በቅርብ ጊዜ የኤክሳይዝ ሕግ ላይ ማሻሻያ አድርጓል:: ይህንን ነጋዴው ሕብረተሰብ ማወቅ አለበት እኛም በስልጠና መርሃግበራችን እናካትታለን በሌላ አነጋገር ቀጣይ በግብር ሕግ ላይ ስልጠና ስንሰጥ በሕጉ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን ጨምረን ስልጠና እንደሰጣለን::

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት እድሎችና ተግዳሮቶች...

ከ ገጽ 4 የዞረ

ከነዳጅ ወጪ ፣ ትራንስፖርት ፣ ወረቀት በማሰቀረት መንግስት የሚያወጣውን ወጪ እንደሚያድን አቶ ሃጂ ይናገራሉ:: በተጨማሪም ስራን በተቀላጠፈ ሁኔታ መጨረስ ያስችላል:: እየተጠናቀቀ ባለው የበጀት አመት በነበረው የጨረታ ሂደት አብዛኞቹ ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት የገቡ ሀገራት የወረቀት ወጪን መቀነስ ችለዋል::

የአገር ውስጥ ጨረታም ሆነ ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ ግዥ ለመፍፀም ከሶስት እስከ አራት ወራት ይወሰድ ነበር:: ምስጋና ለኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሰርዓት ፣ ቀደም ሲል ሶስትና አራት ወራት የሚወሰደውን የጨረታ ሂደት በሃያ ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ ተችሏል:: ከዚህም አለፍ ሲል ሁሉንም የንግድ ማህበረሰብ ያለ ዘር ፣ ሃይማኖት ፣ ትውውቅ አንዱን ከአንዱ ሳያበላልጥ እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖርታል ነው:: አሁን ላይ በኢትዮጵያ የሚስተዋለው ከፍተኛ የገቢያ ዋጋ መለዋወጥ ጋር ተያይዞ በገዥና በአቅራቢ መካከል ያለመግባባት ሲፈጠር ይታያል:: ጨረታው የወጣበት ጊዜና አሸናፊው እቃውን አሰረክብ የሚባልበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ልዩነት ይፈጥራል:: ይህም አቅራቢንና ገዥን ሲያወዛግብ መቆየቱን አስታውሰው ፤ የኤልክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ስርዓት ፈጣንና በአጭር ጊዜ የሚከናወን በመሆኑ ይህንን ችግር እንደሚቀርፍ ያላቸውን እምነት አቶ ሃጂ ገልፀዋል::

የኢትዮጵያ የመንግስት ግዥና ንብረት አሰተዳደር ባለሰልጣን ደረጃ በደረጃ የመንግስት ተቋማትን ወደ ኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ስርዓት ለማስገባት እየሰራ ይገኛል:: አሁን ላይ በሀገሪቱ ከሚገኙ 169 የፌደራል መንግስት ተቋማት ውስጥ 74ቱን ወደ ስርዓቱ ማስገባቱን ጠቅሰው ፤ በ2016 በጀት አመት ቀሪ ዘጠና አምስት የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ እንዲገቡ የሚያደርግ ሲሆን ፤ የክልል የመንግስት ተቋማትን በ2017 ሙሉ ለሙሉ ወደ ኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት ለማስገባት ውጥን መኖሩን የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሰልጣን መረጃ ያመለክታል::

# አዲሱ የንግድ ህግ ለቢዝነስ እንቅስቃሴ ያለው አንደምታ...




**በአሸናፊ ምትኩ**

በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያትና መንግስታት የተለያዩ የንግድ ህጎችና አዋጆች ወጥተው ተተግብረዋል። ከቀድሞው የንጉሳዊ አገዛዝ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የዘለቁ የንግድ ህጎችና አዋጆች የንግድ ስራዎች ህግና ደንብን ተከትለው እንዲሰሩ የበኩላቸውን አስተዋጾ አድርገዋል። እነዚህ የንግድ ህጎችና አዋጆች የንግዱን ማህበረሰብ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ሲጠቅሙትም ሆነ ሲጎዱትም ተስተውሏል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በተለያዩ ጊዜያት የሚወጡ ህጎችና አዋጆች ከመውጣታቸውም ሆነ ከወጡ በኋላ የንግዱን ማህበረሰብ በማወያየት ህጎች እንዲሻሻሉና በአግባቡ ተግባራዊ እንዲደረጉ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ምክር ቤቱ እንዲህ አይነት የፖሊሲ እና የአድቮኬሲ ስራዎችን ለማከናወን ይረዳው ዘንድ የውይይት መድረኮችን በማመቻቸት የንግዱ ማህበረሰብ በንግድ ነክ ህጎችና አሰራሮች እንዲሁም ተግዳሮቶች ዙርያ እንዲወያይና ንቃተ ህሊናው ከፍ እንዲል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል።

የዚህ አንዱ አካል የሆነውና በአዲሱ የንግድ ህግ ዙርያ የተደረገው የምክክር መድረክ አንዱ ነው። ይህ የውይይት መድረክ የንግዱ ማህበረሰብ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ በብሄራዊና በአለምአቀፍ መድረኮች ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህ የውይይት ርእስ አዲሱ የኢትዮጵያ የኩባንያ ህግ በቢዝነስ ምስረታና አሰራር ላይ ያለውን እንደምታ የተመለከተ ሲሆን በአዲሱ የንግድ ህግ ዙርያ ረዳት ፕሮፌሰር ፍቃዱ ጴጥሮስ ለንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በዚህ ርእሰ ጉዳይም ውይይት የተደረገ ሲሆን ሀሳቦችና አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

አዲሱ የንግድ ህግ ከወጣ ሁለት አመት የሞላው ሲሆን አራት አዳዲስ ነገሮችን ይዞ እንደመጣ ንግግራቸውን የጀመረቱት አቶ ፍቃዱ ጴጥሮስ እነዚህን አንድ በአንድ አብራርተዋል። የመጀመርያው በአዲሱ የንግድ ህግ ላይ አዳዲስ ኩባንያዎችን የተመለከቱ ህጎች ይፋ ተደርገዋል በማለት ተናግረዋል። ነጋዴው ምን ያህል እንዚህ ያውቃቸዋል እና ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድን የተመለከቱ ጉዳዮች ተካተዋል። በሶስተኛ ደረጃ በኩባንያ ውስጥ የአነስተኛ ባለአክሲዮኖች መብትን የተመከለቱ ህጎች ተካተዋል።

በ1952 አ.ም የወጣው የንግድ ህግ ከረጅም አመታት በኋላ በ2013 አ.ም ለመጀመርያ ጊዜ የተሻሻለ ሲሆን በወቅቱ የነበሩ የንግድ ማህበር አይነቶች ስድስት ሲሆኑ በተለይ ለንግዱ ማህበረሰብ አስፈላጊ የሆነው ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን የተመለከተ ጉዳይ በአዲሱ የንግድ አዋጅ ላይ መካከተቱን ጽሁፍ አቅራቢው አስረድተዋል። በዚህ አዋጅ ሀላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እንዲካተት ተደርጋል ብለዋል ጥናት አቅራቢው። ነገር ግን በአዲሱ አዋጅ ሁሉንም የንግድ ተቋማት የሚመለከት አይደለም የሚል ሀሳብ አንስተዋል አቶ ፍቃዱ። በዋናነት ይህ ታሳቢ ያደረገው የሙያ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን የሚመለከት እንደሆነ ተናግረዋል። ከነዚህ ተቋማት ጋር የሚሰሩ ሰዎች እነሱ ወይም ማህበረሰቡ ሊጠይቀው የሚችለው እዳ መጠን ተገዳቧል ማለት ነው ስለዚህ እነዚህ አካላት ኢንሹራንስ እንዲገዙ አዋጁ ያዛል። የዚህ ኢንሹራንስ ዋና ጥቅም ደንበኞች ጉዳት ቢደርስባቸው ኢንሹራንስ የማግኘት መብት እንዳላቸው ተጠቁማል።

በሁለተኛ ደረጃ በአዲሱ የንግድ ህግ ላይ የተካተተው ጉዳይ የባለ አንድ አባል ፒኤልሲ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ቀደም አንድ ፒኤልሲ ለማቋቋም አባላት ሁለት እንዲሆኑ ይገደዱ ነበር። በመሆኑም ወደ ንግድ ስራ የሚገቡ ግለሰቦች ሳይወዱ በግዳቸው ሁለት እና ከዛ በላይ ለመሆን ይገደዱ እንደነበር ጥናት አቅራቢው አቶ ፍቃዱ ጴጥሮስ አስረድተዋል። ነገር ግን በዚህ አዲስ አዋጅ አንድ ግለሰብ ፒኤልሲ የማቋቋም መብት እንዳለው ይደነግጋል ብለዋል አቶ ፍቃዱ።

ሌላው በዚህ የንግድ ህግ ውስጥ የመጣው ለውጥ ከዳይሬክተሮች ቦርድና አሰራር ጋር ተያይዞ የተቀመጠው ነው። በተለይም ለአክሲዮን ማህበራት የዳይሬክተሮች ቦርድን በሁለት መክፈል ይቻላል የሚለው ድንጋጌ አንዱ ነው በማለት ይገልጻሉ አቶ ፍቃዱ። ይህ አዋጅ የዳይሬክተሮችን ቦርድ በሁለት በመክፈል አንደኛውን ተቆጣጣሪ ቦርድ ሌላኛውን ደግሞ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ በማለት ለሁለት ይከፍለዋል ብለዋል የህግ ባለሙያው። አዲሱ የንግድ ህግ ለቦርድ ዳይሬክተርነት ብቃት ያላቸው ግለሰቦች በቦርድነት ለመምረጥ መብት ይሰጣል ብለዋል የህግ ባለሙያው። ነገር ግን ቀደም ባለው የንግድ ህግ ላይ አንድ ሰው የቦርድ አባል ለመሆን ባለ ሀብት መሆን አለበት ይህ ደግሞ የዜጎችን እውቀት ሳይሆን ያላቸውን የሀብት ብዛት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ሲሆን ከእውቀት ይልቅ በንብረት ላይ ትኩረት ማድረጉ ኩባንያዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ እንደነበር የዚህ ጥናት አቅራቢ የሆኑት አቶ ፍቃዱ ያስረዱት።

ከቦርድ አወቃቀር ጋር በተያያዘ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲሱ ህግ የቦርድ አሰራር እንዲኖረው ያደረገ ሲሆን ቀደም ባለው የንግድ ህግ ግን ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቦርድ አሰራርን የሚፈቅድ እንዳልነበር እና የመብት ጥሰት ሲያስከትል እንደነበር ጥናት አቅራቢው ተናግረዋል።

ከአነስተኛ ባለአክሲዮኖች ጥበቃ ጋር ተያይዞ በአዲሱ ህግ የተካተቱ ነገሮች እንዳሉ የተጠቆመ ሲሆን ዝቅተኛ ባለአክሲዮኖችን መብት ይከላከላል። የዚህ ዋና መነሻ ህጉ ባለ ሀብቶችን የሚጠብቅ ሲሆን ባለሀብቱ በመተማመን ገንዘቡን ኢንቨስት ያደርጋል በማለት አቶ ፍቃዱ የሚናገሩት። ነገር ግን በቀድሞው የንግድ አዋጅ ትልልቅ ድርሻ ያላቸው ባለሀብቶች አስተዳደርን የመሾም አቅም የነበራች ሲሆን አሁን የተሻሻለው ህግ ላይ ግን በትልልቅ ባለ አክሲዮኖች ላይ ጠበቅ ያለ ህግን ይደነግጋል ብለዋል አቶ ፍቃዱ። ይህ የንግድ ህግ ኩባንያውን ከሚመሩ ሰዎች ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች ከኩባንያው ጋር የሚያደርጉትን ግብይት ይቆጣጠራል በማለት ገልጸዋል። ነገር ግን የቀድሞው የንግድ ህግ ከኩባንያው ጋር ዝምድና ያላቸው ሰዎች የሚያደርጉት ግብይት በመጀመርያ ደረጃ ቦርድ ሊፈቅድ ይገባል ይል ነበር በአዲሱ የንግድ ህግ ግን በተገበያያዎች መካከል ያለውን ግነኙነት በሁለት ይከፍለዋል። አንደኛው ትልልቅ ግብይቶች ከማህበሩ ካፒታል ከአስር በመቶ በላይ ዋጋ ያለው ከሆነ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲፈቅድ ያስገድዳል። ነገር ግን ግብይቱ ከማህበሩ አጠቃላይ ካፒታል አስር በመቶ በታች ከሆነ ቦርዱ ለኦዲተሮች ያሳውቃል ኦዲተሮች ደግሞ ልዩ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ያደርግ ነበር።

አዲሱ የንግድ ህግ ከኩባንያ ጋር የተዛመደ ሰው ከፍተኛ ቁጥጥር እንደሚደረግበት ያስገድዳል። ከማህበሩ ካፒታል ከአስር በመቶ በላይ ያላቸው ባለሀብቶች እንደ ተዛማጅ ፓርቲ ይቆጠራሉ በማለት የህግ ባለሙያውና ጥናት አቅራቢ የሆኑት አቶ ፍቃዱ የሚናገሩት።

አዲሱ የንግድ ህግ ልዩ ምርመራዎችን ይፈቅዳል በማለት ቀደም ካለው ህግ ጋር ያለውን ልዩነት ያስረዳሉ ጥናት አቅራቢው። ይህንንም ሲያብራሩ ባለአክሲዮኖች ከፈለጉ የትኛውንም ግብይት ምርመራ እንዲደረግበት የመጠየቅ መብት ይሰጣል። ይህ ግልጽነት እንዲሁም ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር አዲሱ የንግድ ህግ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# አዲሱ የንግድ ህግ ለቢዝነስ...

ከ ገጽ 10 የዞረ

ወሳኝ ድርሻ እንዳለው አቶ ፍቃዱ የሚናገሩት፡፡
አዲሱ የንግድ ህግ ለአነስተኛ ባለ አክሲዮኖች መረጃ እንዲያገኙ ይፈቅዳል ያሉ ሲሆን የድሮ የንግድ ህግ ለባለአክሲዮኖች የሚፈቅደው መረጃ ከድርጅቱ ማግኘት የሚሉት የባለ አክሲዮኖቹን ዝርዝር ፤የባለፉትን ሶት አመታት የነበሩ ቃለ ጉባኤ የማግኘት መብትን እና በዚህ አመት የሚቀርበውን የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርትን ብቻ የማግኘት መብትን ነበር የሚፈቅደው፡፡ ነገር ግን አዲሱ የንግድ ህግ ተጨማሪ አዳዲስ መረጃዎችን ውሎችን የማግኘት መብትን ይሰጣል በማለት የአዲሱን ህግ ከቀድሞ የንግድ ህግ ጋር በማነጻጸር አስረድተዋል፡፡

በአዲሱ የንግድ ህግ ዙርያ ከተሳታፊዎች አስተያየቶችና ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ከዚህ ቀደም በነበረው የንግድ ህግ ምክንያት ባለሀብቶች ከማይፈልጉት ሰው ጋር ተጣምው እንዲሰሩ ይገደዱ እንደነበር የተናገሩት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአርቢትሬሽን ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አቶ ዮሀንስ ወ/ገብርኤል ናቸው፡፡

አዲሱ የንግድ ህግ በንግድ ግብይት ላይ የሚደረገውን ሙስና እና በዝምድና የሚሰሩ ግብይቶችን ይከላከላል የሚል ሀሳብ አንስተዋል፡፡ በተለይም ይህ የግብይት ችግር አንዱ ተግዳሮት እንደሆነ በመግለጽ፡፡ ከዚህም ባለፈ አዲሱ የንግድ ህግ የኪሳራ ህግ ማካተቱ የንግድ ተቃማት ሲያጋጥማቸው የሚችለውን ኪሳራ በምን አይነት መልኩ እንደሚያስተናግዱት አካታል ብለዋል፡፡ ነገር ግን አዲሱ የንግድ ህግ የራሱ የሆኑ ተግዳሮቶች አሉት ያሉት አቶ ዮሀንስ አዲሱ የንግድ ህግ የአክሲዮን ሽያጭ ድርሻ ላይ ክፍተት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ ይህ ለወደፊቱ በስቶካ ማርኬት ገበያ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

በዚህ የምክክር መድረክ ላይ ከተነሱት አስተያየቶች መካከል የቦርድ አባላት ሚና ከአስፈጻሚዎች ጋር እንዲቀላቀል ሆኗል የሚሉ ይገኙበታል፡፡ ብቃት ያላቸውን የቦርድ አባላትን በተለፈገው ጊዜ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ሀሳብ ተሰንዝሯል፤ አንድ ሰው በፒኤልሲ እንዲደራጅ ህጉ የሰጠው መብት አሁን ላይ በአዲሱ የንግድ ህግ ተግባራዊ እየሆነ አይደለም የሚሉ ቅሬታዎች ተነስተዋል፡፡

አዲሱ የንግድ ህግ የዘመናዊ ወይም የኢኮሜርስ ግብይትን እንዴት በምን አይነት መልኩ ቃኝቶታል፤የጥምር ቦርድ አሰራሮች የትኞቹን የንግድ ተቋማት የሚመለከት እንደሆነ በግልጽ ቢቀመጥ፤ ድርጅቶች ኪሳራ ሲያጋጥማቸው በምን አይነት መልኩ ሊዘጉ እንደሚችሉ ህጉ በግልጽ ማስቀምጥ ቢችል ጥሩ ነው የሚሉ ምልከታዎች በዚህ የውይይት መድረክ ተካተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ከአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ ለመሥራት ሥምምነት ተፈራረመ

ከ ገጽ 3 የዞረ

በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የረጅም ዓመታት ልምድ ካካበተው ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጋር በጋራ መሥራቱ ሁነኛ መፍትሄ ነው ሲሉ አክለዋል፡፡

ምክር ቤቱ በቀጣናው የንግድ ትስስርን ማሳለጥ፣ በአረንጓዴ ኢኮኖሚ፣ የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የጀመራቸው እንቅስቃሴዎች እንዲሳለጡ ሥምምነቱ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

ዘመናዊ አሰራር የሆኑት እንደ ካፒታል ገበያ ላይ ምክር ቤቱ በስፋት ለመሥራት ውጥን እንዳለው የገለጹት አቶ ሺበሺ በዚህ በኩል ከኢዜአ ጋር አብረን መስራታችን ጉዞውን የተቃና ያደርገዋል ነው ያሉት፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ጸሃፊ ልዩ አማካሪ አቶ ሲሳይ ታደሰ በበኩላቸው ምክር ቤቱ ከኢዜአ ጋር በትብብር መሥራቱ የግሉ ዘርፍ ማነቆዎች እንዲፈቱ ማድረግ ላይ አዎንታዊ አሻራ የሚያሳርፍ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሥምምነቱ ማዕቀፍ ላይ የተቀመጡ ጉዳዮች ወደ መሬት እንዲወርዱ ምክር ቤቱ በቁርጠኝነት እንደሚሰራም አረጋግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ነጋሲ አምባዬ በበኩላቸው ሁለቱ ተቋማት የፈረሙት ሥምምነት ንግድና ኢንቨስትመንትን በማነቃቃት ረገድ ያለው ፈይዳ ከፍ ያለ መሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

“ኢኮኖሚው ሲያድግ የገጽታ ግንባታውም በዛው ልክ ይጨምራል” ያሉት አቶ ነጋሲ የገጽታ ግንባታና የኢኮኖሚ ዕድገቱን የሚያፋጥኑ ተግባራትን በጋራ ለመከወን ተስማምተናል ብለዋል፡፡

ኢዜአ ዜናዎችን ተደራሽ ለማድረግ ከበርካታ መገናኛ ብዙሃን ጋር ሥምምነት መፈረሙን አስታውሰው ምክር ቤቱ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች የበለጠ ለማስተዋወቅና ተደራሽ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑንም አረጋግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የህዝብ ግንኙነትና ስትራቴጂያዊ አጋርነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዮሃንስ ወንድራድ እንደገለጹት ተቋማቱ ያደረጉት ሥምምነት የግልና የመንግሥት አጋርነትን የማጠናከር ሚናው የላቀ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በሥሩ በርካታ የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች መኖራቸውን ጠቁመው ከዚህ አንጻር ሥምምነቱ በከተማው ብሎም በአገሪቱ ያሉ የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራዎች ለማስተዋወቅ ትልቅ አስተዋጽዖ አለው ብለዋል፡፡

# ብቁ እና ተወዳዳሪ ኩባንያዎችን ለማፍራት....

ከ ገጽ 9 የዞረ

**ንግድና ልማት፡** ከመደበኛዎቹ በተጨማሪ የሚሰጡ ስልጠናዎች ካሉ፤

**አቶ ደሳለኝ፡** አሉን፡፡ እነዚህ ስልጠናዎች ፈረንጆች (Soft Skill) የሚሏቸው ናቸው፡፡ በየጊዜው አዳዲስ የቢዝነስ ግኝቶች፤አዳዲስ አስተሳሰቦችን ፤የቢዝነስ ጥበባትን እየተከታተልን ስለጠና እንሰጣለን፡፡

**ንግድና ልማት፡** ስልጠናው ለነጋዴው ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ ምን እየተሰራ ነው ?

**አቶ ደሳለኝ፡** በአገራችን የግል ዘርፍ ገና በማደግ ላይ የሚገኝ ዘርፍ ነው፡፡ የቢዝነስ ዘርፍ ደግሞ ሁሉ በእንቅስቃሴ እና በለውጥ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ነጋዴው ሕብረተሰብ በራሱ ካዳበረው አውቀት እና ክህሎት በተጨማሪ እራሱን እና ሰራተኞቹን በስልጠና ማብቃት እና ጊዜው በሚጠይቀው ልክ ዘምኖ መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሁሉም በቢዝነስ ዓለም ያሉ ዜጎች የስልጠናው ተሳታፊ ቢሆን ደስ ይለናል፡፡ ዛሬ ላይ ንግድ በእውቀት እና በጥበብ የሚመራ ሥራ ሆኗል፡፡ ስለዚህ አዲስ ቻምር የሚሰጠውን ስልጠና ከመደበኛ የመገናኛ ብዙሃን በተጨማሪ በንግድ ም/ቤታቸን የማሕበራዊ ትስስር ገጾቻችን ላይ ለሁሉም ባለድርሻዎች እና እናሰራጫለን፡፡ በምክር ቤታችን የሬዲዮ፤የተሌቪዝን እና ጋዜጣ ላይ ዝግቶች አማካኝነት የስልጠና መረጃዎችን እንሰጣለን፡፡ በተለይ የአዲስ ቻምበር ድረገጽ እና ማስ ሜይል አማካኝነት ስልጠና ፈላጊዎች በማኝኛውም ጊዜ እና ከሉበት ቦታ ሆነው መረጃዎችን እናደርሳለን፡፡

**ንግድና ልማት፡** እናመሰግናለን፤
**አቶ ደሳለኝ፡**
እኔም አመስግናለሁ፤እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER